የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ
መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ



www.ehrc.org

# የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርት

ከሰኔ 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርት

## (ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም.)

የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

# ማውጫ


የኢሰመኮ ተጠባባቂ ዋና ኮሚሽነር መልእክት .......... i
አንኳር ጉዳዮች .......... iv
ምክረ ሐሳቦች .......... v
ክፍል አንድ .......... 1
መግቢያ .......... 1
የመረጃ አሰባሰብ ሥነ-ዘዴ .......... 1
ክትትልና ምርመራ የተከናወነባቸው አካባቢዎች .......... 2
ተግዳሮቶች .......... 5
ክፍል ሁለት .......... 8
የሕግ ማዕቀፍ .......... 8
ክፍል ሦስት .......... 15
በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የመፈናቀል ሁኔታ፣ ቁልፍ እመርታዎች እና አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች .......... 15
አጠቃላይ የመፈናቀል ሁኔታ መረጃ .......... 15
ቁልፍ እመርታዎች .......... 17
ዋና ዋና አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች .......... 18
ግልጽ የሕግ ማዕቀፍ እና ተቋማዊ አደረጃጀት .......... 18
የምዝገባ፣ ሰነድ የማግኘት እና የመንቀሳቀስ መብቶች .......... 19
የጸጥታ፣ ደኅንነት እና ፍትሕ የማግኘት መብት .......... 22
የሰብአዊ ድጋፍ የማግኘት መብት .......... 23
ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች .......... 28
የቤት፣ መሬት እና ንብረት መብት .......... 30
ዘላቂ መፍትሔ .......... 32
ክፍል አራት .......... 37
ማጠቃለያ እና ምክረ ሐሳብ .......... 37
ማጠቃለያ .......... 37
ምክረ ሐሳቦች .......... 38

# የኢሰመኮ ተጠባባቂ ዋና ኮሚሽነር መልእክት

ይህ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ሦስተኛው በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ ያተኮረ ዓመታዊ የዘርፍ ሪፖርት ሲሆን፣ ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ጊዜ ይሸፍናል። ኢሰመኮ ሰኔ 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ይፋ ካደረገው ሦስተኛው የኢትዮጵያ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ ባከናወናቸው ልዩ ልዩ ተግባራት፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች ሁኔታን በተመለከተ የለያቸውን መልካም ጅማሮዎች፣ አሳሳቢ ሁኔታዎችን እንዲሁም በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሊተገበሩ የሚገባቸውን ምክረ ሐሳቦች አካቷል።



**ራኬብ መሰለ**
**ተጠባባቂ ዋና ኮሚሽነር**

ኢሰመኮ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ሰብአዊ መብቶች አንዱ የትኩረት አቅጣጫ በማድረግ ላለፉት 4 ዓመታት ወቅታዊ እና ቀጣይነት ያላቸው

የሰብአዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ፣ ግንዛቤ ማስጨበጥ እንዲሁም ውትወታ ሲያከናውን ቆይቷል። ይህ ሪፖርት በሚሸፍነው ጊዜም በአማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሐረሪ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሊ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች እንዲሁም ትግራይ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች አያያዝን በተመለከተ በአጠቃላይ 13 ክትትሎች እና 1 ምርመራ አካሂዷል። በዚህም ተፈናቃዮች የሚገኙባቸው 31 የመጠለያ እና ጊዜያዊ ማቆያ ጣቢያዎችን፣ 13 ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩባቸውን፣ 3 ወደቀድሞ ቀያቸው የተመለሱባቸውን እንዲሁም 3 ወደ ሌላ ቦታ ተዘዋውረው የሚኖሩባቸውን አካባቢዎች ለመሸፈን ተችሏል። በተጨማሪም በ2015 ዓ.ም. ያደረገውን ክትትልና ምርመራ መሠረት በማድረግ የምክረ ሐሳብ አፈጻጸም ክትትል እንዲሁም ውትወታን አከናውኗል። በዚህም በአጠቃላይ የ333,889 ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለመፈተሽ ተችሏል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መፈናቀል እንዲሁም ልዩ ፍላጎትን ያላማከለ የጥበቃ እና ድጋፍ አገልግሎት በተለየ ሁኔታ ለመብት ጥሰት ተጋላጭ በሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች (በተለይም ከቤተሰባቸው ለተለዩ እና ብቻቸውን ላሉ ሕፃናት፣ ለነፍሰ-ጡሮች፣ ጨቅላ ሕፃናት ላሏቸው እናቶች፣ ለአረጋውያን እና ለአካል ጉዳተኞች) ላይ የሚያስከትለውን የተወሳሰበ ችግር ለመለየት ተችሏል።

በክትትል እና ምርመራ በተለዩ ግኝቶች ላይ በመመርኮዝም የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ሰብአዊ መብቶች ለማስፋፋት፣ ለማስከበር እና ለማሟላት ይቻል ዘንድ ኢሰመኮ ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በርካታ የምክክር መድረኮችን፣ የሁለትዮሽ ውይይቶችን፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲሁም የውትወታ ሥራዎችን አከናውኗል። በዚህም የተወሰኑ ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን በመልካም ተሞክሮነት ማሳያ የሚሆኑት በዚህ ሪፖርት ውስጥ ተካተዋል። በተለይም በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ መጽደቁ እና የሀገራዊ ምክክር ሂደቱ መጀመሩ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ከመስጠት አንጻር የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በአዎንታዊ መልኩ የሚጠቀሱ ናቸው። የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው የእውነት ማውጣት ሂደቱ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ሌሎች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ

የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ባካተተ መልኩ እንደሚተገበር እንደ አንድ የፖሊሲ አቅጣጫ ማስቀመጡ እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሽግግር ፍትሕ ሂደት ውስጥ በአግባቡ መስተናገዳቸውን፣ ወደ ቦታቸው መመለሳቸውን እና መሰል መብቶች የተጠበቁላቸው ስለመሆኑ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ የሰላም ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት አድርጎ በግልጽ ማስቀመጡ የሚበረታታ ነው፡፡

በሌላ በኩል በአፍሪካ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃና ድጋፍን አስመልክቶ የጸደቀው የአፍሪካ ኅብረት ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) በሚጠይቀው መሠረት፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች በአግባቡ እንዲከበሩ፣ እንዲጠበቁ እና እንዲሟሉ መንግሥት ብሔራዊ የማስፈጸሚያ ረቂቅ ሕግን በማጽደቅ እንዲሁም ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የተሟላ ድጋፍና ጥበቃ እንዲደረግ የሚያስተባብር በግልጽ ሥልጣን የተሰጠው ተቋም በማቋቋም/በመሰየም ወደ ሥራ ማስገባት አሁንም አፋጣኝ መፍትሔ የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

በኢትዮጵያ አብዛኛው መፈናቀል እየተከሰተ ያለው ኃይል በተቀላቀለባቸው ግጭቶች እና በጦርነት ምክንያት በመሆኑ ግጭቶችን በአፋጣኝ ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ መፍታት እና እንዳይባባሱ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፤ መፈናቀልን ለመከላከል እና በዘላቂነት መፍትሔ ለመስጠት ወሳኝ በመሆናቸው ትኩረት ሰጥቶ መተግበር ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት መፈናቀል እንዳይከሰት የቅድመ-አደጋ መከላከል ሥራዎች፣ መፈናቀሉ በተከሰተ ጊዜም በአደጋ እና ድኅረ-አደጋ ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች በአፋጣኝ እና በተሟላ ሁኔታ መወሰድ አለባቸው፡፡ ለተፈናቃዮች የሚደረጉ ድጋፎችን ጊዜያዊ የአደጋ ጊዜ የሰብአዊ ድጋፍ ጉዳይ ብቻ አድርጎ መውሰድ ሌላኛው የሚጠቀስ ተግዳሮት ሲሆን፤ ተፈናቃዮች ላሉበት ሁኔታ ዘላቂ መፍትሔ የማያስገኝ ከመሆኑም በላይ ለባሰ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ይዳርጋቸዋል፡፡ በተለይም ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ሳያገኙ በተራዘመና ውስብስብ በሆነ የመፈናቀል ሁኔታ (Protracted Displacement) መቆየታቸው፣ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭነታቸውን የሚጨምርና ችግሩን የሚያባብስ እንዲሁም በሥራ ተሰማርቶ እራሱን መቻል የሚችል የሰው ኃይልን የድጋፍ ጠባቂ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም እንደ ሀገር ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት በሚሠሩ ሥራዎች እና በተገኙ ውጤቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው፡፡ ስለሆነም መፈናቀልን ለመከላከል፣ ለተፈናቃዮች ተገቢው ጥበቃና ድጋፍ መቅረቡን ለማረጋገጥ እንዲሁም ዘላቂ መፍትሔን ለማመቻቸት፤ የፖለቲካ ፈቃደኝነትና ቁርጠኝነትን በግልጽ በሚያሳይ መልኩ መንግሥት ለችግሩ ተገቢውን ዕውቅናና በቂ ትኩረት በመስጠት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት ይኖርበታል፡፡

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ያሉ ተፈናቃዮችን ወደቀድሞ ቀያቸው ለመመለስ በመንግሥት የተጀመሩ ጥረቶች የሚበረታቱ ቢሆንም፣ ተፈናቃዮች እንደማንኛውም ዜጋ ወይም ነዋሪ በየትኛውም የሀገሪቷ አካባቢ ተንቀሳቅሰው የመኖር መብታቸው ሊከበርላቸው የሚገባ በመሆኑ፣ ተፈናቃዮችን በዘላቂ ሁኔታ ለማቋቋም ወደ ቀድሞ የመኖሪያ ቦታቸው መመለስ ብቸኛው አማራጭ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም፡፡ በተመሳሳይ ተፈናቃዮች ወደ ቀድሞ ቀያቸው እንዲመለሱ ለማድረግ የጥበቃና የድጋፍ ተግባራትን ማቋረጥ እንዲሁም ተጠልለውባቸው የነበሩ ቦታዎችን መዝጋት/ማፍረስ ለዳግም መፈናቀል የሚዳርጋቸው ነው፡፡ በመሆኑም ዘላቂ መፍትሔን መፈለግ የሰብአዊ ድጋፍን ከማቅረብ እኩል ሊታሰብበት ይገባል፡፡

መፈናቀልን መከላከል፣ ለተፈናቃዮች ጥበቃና ድጋፍ መስጠት እንዲሁም ዘላቂ መፍትሔን ማመቻቸት በዋናነት የመንግሥት ኃላፊነት ቢሆንም ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ ድጋፍ ድርጅቶች፣ ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሁም የግል ሲክተሩ በተቀናጀ መልኩ የየበኩላቸውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡

በተጨማሪም መፈናቀልን ባስከተሉ እንዲሁም መፈናቀልን የመከላከል ወይም ምላሽ የመስጠት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡ አካላት ላይ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሠራር መዘርጋትና መተግበር ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ኢሰመኮ በተለያየ ጊዜያት የሚሰጣቸውን ምክረ ሐሳቦች በመቀበል የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለማሻሻል የተደረጉ ጥረቶች የሚበረታቱ እና ተጠናክረው ሊቀጥሉ የሚገባቸው ሲሆኑ፣ በተለይም በረቂቅ ደረጃ የሚገኘው ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃና ድጋፍ ለማድረግ የተዘጋጀው ብሔራዊ የሕግ ማዕቀፍ በአጭር ጊዜ ጸድቆ ወደ ተግባር እንዲገባ፤ እንዲሁም የሽግግር ፍትሕ እና የሀገራዊ ምክክር ሂደቶች የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን መብቶችና ተሳትፎ በሚያረጋግጥ ሁኔታ እንዲተገበሩ ሁሉም ባለድርሻዎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቀርባለሁ።

# አንኳር ጉዳዮች

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ሦስተኛውን የኢትዮጵያ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ሰኔ 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ይፋ ማድረጉ ይታወሳል። ከዚህ በተጨማሪነት በዚህ ሦስተኛው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በተከናወኑ ክትትሎች እና ምርመራ የተለዩ መልካም ጅማሮዎች፣ አሳሳቢ ጉዳዮች እና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሊተገበሩ የሚገባቸው ምክረ ሐሳቦች በዝርዝር ተካተዋል። ኢሰመኮ ሁለተኛውን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርት በጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም. ይፋ ማድረጉ የሚታወስ ሲሆን፤ በዚህ በሦስተኛው የሪፖርት ጊዜም የሀገር ውስጥ መፈናቀል እና የተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ አሳሳቢ ችግር ሆኖ ቀጥሏል።

የሀገር ውስጥ መፈናቀል ሁኔታን በቅርበት የሚከታተለው ዓለም አቀፍ የፍልሰት ድርጅት (International Organization for Migration-IOM) እ.ኤ.አ. በግንቦት ወር 2024 ያወጣው ሪፖርት እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቁጥር 3.3 ሚሊዮን ደርሷል። ከእነዚህ ውስጥ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በየጊዜው በሚከሰቱ ማንነትን መሠረት ያደረጉ የታጠቁ ቡድኖች ጥቃቶች፣ በመንግሥት እና በታጠቁ ቡድኖች መካከል በሚደረጉ ግጭቶች እንዲሁም ዘላቂ ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ መፍትሔ ባልተሰጠባቸው የወሰን ይገባኛል እና የማንነት ይከበርልኝ ጥያቄዎች ምክንያት በሚፈጠሩ ግጭቶች ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ከፍተኛውን ቁጥር (68.7 ከመቶ) ይይዛሉ። ቀሪዎቹ እንደ ጎርፍ እና ድርቅ ባሉ ተፈጥሯዊ አደጋዎች እንዲሁም በልማት ፕሮጀክቶች እና ሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች የተፈናቀሉ ናቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ተፈናቃዮች ውስጥ 56 ከመቶ የሚሆኑት ከ1 ዓመት፤ 23 ከመቶ የሚሆኑት ከ2 እስከ 4 ዓመት እና 11 ከመቶ የሚሆኑት ከ5 ዓመት በላይ በተራዘመ የመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ።

ይህ የዘርፍ ሪፖርት በሚሸፍነው ጊዜም 13 የተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትሎች እና 1 ምርመራ በ8 ክልሎች በማከናወን በአጠቃላይ የ333,889 ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለመፈተሽ ተችሏል። በዚህም ተፈናቃዮች የሚገኙባቸው 31 የመጠለያ እና ጊዜያዊ ማቆያ ጣቢያዎችን፣ 13 ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩባቸውን፣ 3 ወደቀድሞ ቀያቸው የተመለሱባቸውን እንዲሁም 3 ወደ ሌላ ቦታ ተዘዋውረው የሚኖሩባቸውን አካባቢዎች ለመሸፈን ተችሏል። በተጨማሪም በ2015 ዓ.ም. በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በተፈናቃዮች የቤት፣ መሬት እና ንብረት መብት ላይ ያደረገውን ምርመራ መሠረት በማድረግ የምክረ ሐሳብ አፈጻጸም ክትትል እንዲሁም ውትወታ ተከናውኗል።

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የተሟላ ጥበቃ እና ድጋፍ ማረጋገጥ የሁሉንም መንግሥታዊ ተቋማት ትኩረትና ትብብር (whole of government approach) የሚፈልግ ቢሆንም፤ በዘርፉ የተሰማሩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን ለማስተባበር እና ለመምራት በሕግ ግልጽ ሥልጣን የተሰጠው አካል አለመኖሩ፤ ለተፈናቃዮች የተሟላ ድጋፍ እና ጥበቃ ለማድረግ በተሰማሩ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሠራር እንዳይኖር አድርጓል። ኢትዮጵያ በአፍሪካ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃና ድጋፍን አስመልክቶ የተደረገውን የአፍሪካ ኅብረት ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) ተቀብላ ያጸደቀች ሲሆን፣ ስምምነቱን ለማስፈጸም ብሔራዊ ረቂቅ ሕግ የተዘጋጀ ቢሆንም ሕጉ ጸድቆ ሥራ ላይ ባለመዋሉ እንዲሁም መፈናቀልን መከላከል የሚችል፣ ለተፈናቃዮች የሚደረጉ የሰብአዊ ድጋፍና ጥበቃ እንዲሁም የዘላቂ መፍትሔ ማፈላለግ ሥራዎችን የሚያስተባብርና በበላይነት የሚመራ ተቋም ባለመኖሩ

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ አሳሳቢ ችግር ሆኖ እንዲቀጥል አስተዋጽዖ አድርጓል።

ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሚደረገው ምዝገባ እና ሰነድ የማግኘት ሥርዓቱ ላይ መሻሻሎች ቢኖሩም አሁንም የአሠራር ክፍተት የሚስተዋልበት እና ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው በመሆኑ፤ ለተፈናቃዮች የሚደረገውን የሰብአዊ ድጋፍ በአግባቡ እንዳይከናወን፣ የተፈናቃዮችን ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ እና ማኅበራዊ አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን ጨምሮ ሌሎችን መብቶች ለመጠቀም እንዳይችሉ አድርጓል። ከዚህም ሌላ ተገቢው ጥበቃ የማይደረግላቸው እና የሲቪልነት ባሕሪን ያልጠበቁ ተፈናቃዮች የሚገኙባቸው መጠለያ/ማቆያ ጣቢያዎች በመኖራቸው የተፈናቃዮች ያለሥጋት በደኅንነት የመኖር እና ከጥቃት የመጠበቅ መብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል።

በተወሰኑ አካባቢዎች ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እንዲሁም ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ ተፈናቃዮችን ልዩ ፍላጎት መሠረት ያደረገ የሰብአዊ ድጋፍ በተለይም በቂ የሆነ የምግብ እና ምግብ-ነክ ያልሆነ ድጋፍ ወቅቱን ጠብቆ አለመቅረብ፤ የሚቀርበው ድጋፍም ቢሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጠንም ሆነ በዐይነት እየቀነሰ መምጣት ወይም ከተቀመጠው መስፈርት በታች መቅረብ ተፈናቃዮችን ለከፋ የሰብአዊ ችግር አጋልጧቸዋል። በተለይም ሴቶች እና ወጣቶችን ራሳቸውን ለጥቃት እና ለጉልበት ብዝበዛ ሊያጋልጡ ወደሚችሉ ሥራዎች እንዲሰማሩ አድርጓቸዋል። በተጨማሪም ተፈናቃዮች ለዓመታት በፀሐይና ዝናብ በተጎዱ የመጠለያ ሸራዎች ውስጥ ከአንድ በላይ ቤተሰቦች በጋራ በተጣበበ ሁኔታ፤ እንዲሁም በትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ለተለያዩ አገልግሎት በተዘጋጁ ንጽሕና በጎደላቸው መጋዘኖች እና ጅምር ሕንፃዎች ውስጥ ለመኖር ስለሚገደዱ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች፣ ለደኅንነት ሥጋት እንዲሁም፤ ሴቶች እና ሕፃናትን ለጾታዊ ጥቃት ተጋላጭ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

በተለያዩ ጊዜያት ነዋሪዎችን ከመደበኛ የመኖሪያ ቦታቸው በኃይል በማፈናቀል የሰው ሕይወት እንዲጠፋ፣ ንብረት እንዲወድም፣ በሰዎች ላይ አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጉዳት እንዲደርስ ያደረጉ ቡድኖች እና ሰዎች በሕግ እንዲጠይቁ አጥጋቢ እርምጃዎች አለመወሰዳቸው የሕግ የበላይነትን እና ተጠያቂነትን የማያረጋግጥ እንዲሁም የተፈናቃዮችን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚነፍግ ነው። ይህም በሀገሪቱ በስፋት የሚስተዋለው ማንነትን መሠረት ያደረገ ሰዎችን በኃይል ማፈናቀል ተግባር ተባብሶ እንዲቀጥል አስተዋጽዖ አድርጓል።

የዘላቂ መፍትሔ አማራጮች በተወሰኑ ክልሎች መተግበር መጀመራቸው የሚበረታታ ቢሆንም የሰብአዊ መብቶች መርሖችን ያልተከተሉ በተለይም የመፈናቀል ምክንያት የሆኑትን የደኅንነት ሥጋቶች ያላስወገዱ፤ ተፈናቃዮችን እና ተቀባይ ማኅበረሰብን ያላሳተፉ፤ የተፈናቃዮችን ፍላጎትና ፈቃድ ያላገናዘቡ፤ በዕቅድ እና በጀት ያልተደገፉ፤ እንዲሁም የተፈናቃዮችን የቤት፣ የመሬት እና የንብረት መብቶችን ከግምት ያላስገቡ በመሆኑ ተፈናቃዮችን በዘላቂነት ለማቋቋም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረም። የተለያዩ የዘላቂ መፍትሔ አማራጮች ቢኖሩም እየተተገበረ ያለው አማራጭ ተፈናቃዮችን ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው መመለስ ላይ ብቻ የተወሰነ ነው።

# ምክረ ሐሳቦች

- የካምፓላ ስምምነት ማስፈጸሚያ ብሔራዊ የሕግ ረቂቅ መንግሥት ልዩ ትኩረት በመስጠት በተፋጠነ ሁኔታ እንዲያጸድቅና ተግባራዊ እንዲያደርግ፤ እንዲሁም በግልጽ ስልጣን የተሰጠው ተቋም በማቋቋም ወደ ሥራ እንዲያስገባ፤ መፈናቀልን ለመከላከል

የሚያስችል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት መቅረጽን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፤

- በተፈጥሮ አደጋ በተለይም በጎርፍ አደጋ ሳቢያ ሊከሰት የሚችለውን መፈናቀል እና የሰብአዊ ቀውስ ለመቀነስ መንግሥት በትምህርት እና ጤና ተደራሽነት እንዲሁም በግብርና ምርቶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ አስቀድሞ በመተንበይ እና በማቀድ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ፤ የትምህርት፣ የጤና፣ የግብርና እና ሌሎች መሠረተ ልማቶች ሲገነቡም አካባቢያዊ ሁኔታን ታሳቢ ያደረጉ እና የአደጋ ሥጋትን በተለይም የጎርፍ አደጋን በዘላቂነት መቋቋም የሚችሉ መሆናቸውን እንዲያረጋግጥ፤
- የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶቻቸውን መጠቀም እና መተግበር እንዲችሉ የሚያስፈልጓቸውን የግል መታወቂያ፣ የወሳኝ ኩነት ሰነዶችን እና ፓስፖርት እንዲያገኙ ወይም በመፈናቀል ሂደት የጠፉ ወይም የተበላሹ ሰነዶቻቸው እንዲተኩላቸው ባሉበት ቦታ አስፈላጊው ሁኔታዎች እንዲመቻቹላቸው፤
- የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የተጠለሉባቸውን ቦታዎች የሲቪልና የሰብአዊነት ባሕሪ እንዲከበር፤ መንግሥት የታጠቁ ቡድኖች ወይም አካላት ወደ እነዚህ ቦታዎች ሰርገው በመግባት ጥቃት እንዳይፈጽሙ ተገቢውን ጥበቃ እና ክትትል እንዲያደርግ፤ እንዲሁም ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ተፈናቃዮችን ለተጨማሪ የመብት ጥሰት የሚዳርጉ ሁኔታዎችን ትኩረት ሰጥቶ በየጊዜው በመከታተል እና በመለየት አስፈላጊውን የደኅንነት እርምጃ እንዲወሰድ፤
- የተፈናቃዮችን የመንቀሳቀስ እና የመኖሪያ ቦታን የመምረጥ መብትን የሚገድቡ ሁኔታዎችን መቅረፍ፣ እንዲሁም በመብቱ ላይ ገደብ የመጣል ውጤት ያላቸውን ተመጣጣኝ፣ አስፈላጊ እና ሕጋዊ ያልሆኑ ውሳኔዎችን በመከለስ ተፈናቃዮች በመብቶቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ መንግሥት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ፤
- በኃይል ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ፍትሕ የማግኘት መብታቸው እንዲከበር ያፈናቀሉ፣ ሕይወት ያጠፉ፣ የአካል ጉዳት ያደረሱ፣ ንብረት የዘረፉ እና የተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በመፈጸም ተሳታፊ የነበሩ አጥፊዎችን በየደረጃው የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል የፍትሕ አካላት በሕግ ተጠያቂ እንዲያደርጓቸው፤
- መንግሥት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ እስከሚቻለው ባለመዘግየት በቂ ምግብና ውሃ፣ መጠለያ፣ የሕክምና እና የጤና አገልግሎቶች፣ ንጽሕና፣ ትምህርት እና ሌሎች አስፈላጊ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ያካተተ የሰብአዊ ድጋፍ የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በማስተባበር እንዲያቀርብ፤ ተገቢ ሆኖ ሲገኝም እነዚህን ድጋፎች ለተቀባይ ማኅበረሰብም እንዲያደርስ፤
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተፈናቃዮች በተለይም ከቤተሰባቸው ለተለዩ እና ብቻቸውን ላሉ ሕፃናት፣ ለሴት የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች፣ ለነፍሰ-ጡሮች፣ ጨቅላ ሕፃናት ላሏቸው እናቶች፣ ለአረጋውያን እና ለአካል ጉዳተኞች ወይም የማይድን/ቋሚ ሕመም ላለባቸው ተፈናቃዮች ልዩ ጥበቃ እና ድጋፍ እንዲደረግላቸው፤ ለተፈናቃይ ሴቶች የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት እንዲሁም ወሲባዊ እና ሌሎች ተያያዥ ጥቃቶች ለደረሰባቸው ተገቢው የሥነ ልቦና እና ማኅበራዊ ድጋፍ እንዲደረግላቸው፤
- መንግሥት እንደ አስፈላጊነቱ ለጋሽ ድርጅቶችን በማስተባበር ጭምር የተፈናቃዮችን ደኅንነትና ሰብአዊ ክብር በጠበቀ ሁኔታ እንዲሁም በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የዘላቂ መፍትሔ አማራጮችን ተግባራዊ እንዲያደርግ፤ እንዲሁም የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ተፈናቃዮች በዘላቂነት ለመቋቋም ስላሏቸው አማራጮች በመረጃ ላይ ተደግፈው መመረጥ እንዲችሉ እንዲያደርግ፤

- ወደ ቀድሞ መኖሪያ ቀያቸው የተመለሱ ወይም ሌላ ቦታ የሰፈሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በዘላቂነት ተቋቁመው እራሳቸውን ማስተዳደር እስኪችሉ ድረስ መንግሥት በቂ፣ ወቅቱን የጠበቀ እና ተደራሽ የሆነ የሰብአዊ ድጋፍ እንዲያቀርብ እና መጠለያ እንዲያመቻችላቸው፤ እንዲሁም የወደሙ መኖሪያ ቤቶችን መጠገን/መሥራት እና የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን ወደነበሩበት በመመለስ ተደራሽ እንዲያደርግ፤
- የመንግሥት ዘላቂ መፍትሔ ዕቅዶችና መርኃ ግብሮች የተፈናቃዮችን የቤት፣ መሬት እና የንብረት መብቶች ከግምት ውስጥ እንዲያስገባ፤ በተለይም ከመሬታቸው ጋር ልዩ ጥገኝነትና ቁርኝት ያላቸው ተፈናቃዮች ወደቀድሞ ቀያቸው በሚመለሱበት እና በሚቋቋሙበት ወቅት በሌሎች ሰዎች ወይም በመንግሥት አካላት የተያዘባቸው መሬት እንዲመለስላቸው ወይም ምትክ እንዲሰጣቸው በተቻለ መጠን አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በሙሉ እንዲወሰዱ፤ ወደሌላ አካባቢ ተዘዋውረው እንዲሰፍሩ ሲደረግም የተፈናቃዮችን የቀድሞ አኗኗር ሁኔታ ከግምት ውስጥ እንዲያስገባ፤
- በተለያዩ መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ እና ለመመለስ በሂደት ላይ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ወደ ተፈናቀሉበት ቦታ እንዲመለሱ ከመደረጉ አስቀድሞ የክልል እና ፌዴራል የመንግሥት አካላት ተቀናጅተው በአካባቢዎቹ የሚስተዋሉ የጸጥታ ሥጋቶችን አስተማማኝ በሚባል ደረጃ መቀረፋቸውን እንዲያረጋግጡ እና የሕግ የበላይነት እንዲያስከብሩ፤ ለተመለሱት ተፈናቃዮችም በአካላቸው እና በንብረታቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጥቃት ለማስቀረት ተገቢው ጥበቃ ማድረግ ይገባል።



Photo credit: EHRC/Media and Comms/Haleluya Abebe

WWW.EHRC.ORG



Photo credit: EHRC/Media and Comms/ Haleluya Abebe

# ክፍል ፩

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ሦስተኛውን ዓመታዊ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ሰኔ 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ይፋ ማድረጉ ይታወሳል። ይህ ሦስተኛው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ዓመታዊ ሪፖርት በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች አያያዝና ጥበቃ ላይ ብቻ የሚያተኩር ሲሆን፤ ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. በተከናወኑ የክትትል፣ የምርመራ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የውትወታ ሥራዎች በ2016 ዓ.ም. በጀት ዓመት የታዩ መልካም ጅማሮዎችን እና እመርታዎችን ለይቷል። በተጨማሪም የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በሕይወት የመኖር፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ፣ እንዲሁም ፍትሕ፣ ሰብአዊ ድጋፍ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን የማግኘት መብቶች ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር ትርጉም ያለው መሻሻል እንዳይኖር ያደረጉ እና መልካም ጅማሮዎችን ወደ ኋላ የሚጎትቱ፣ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መፍትሔ ሊያገኙ እና ሊሻሻሉ የሚገባቸው አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችንም በዝርዝር አካቷል።

ኢሰመኮ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. በራሱ ተነሳሽነት እንዲሁም ከባለመብቶች/ተጎጂዎች የቀረቡለትን አቤቱታዎች መነሻ በማድረግ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው መጠለያ ጣቢያዎች እና አካባቢዎች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ክትትል እና ምርመራ አከናውኗል። በክትትልና ምርመራው በተለዩ የተቋማዊ፣ የሕግ ማዕቀፍና የአሠራር ክፍተቶች እንዲሁም በተሰጡ ምክረ ሐሳቦች ላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልል እና የፌዴራል መንግሥት አካላት ጋር ውይይቶች በማድረግ፤ ምክረ ሐሳቦችን ለመፈጸም የሚያስችሉ ዝርዝር ተግባራት በማስቀመጥ እና አፈጻጸማቸውን በመከታተል የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እንዲሻሻል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እና ውትወታ ተደርጓል። በዚህም ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተገቢውን ጥበቃ እና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ግልጽ የሕግ ማዕቀፍ እና ተቋማዊ አደረጃጀት የመኖር አስፈላጊነት እና የዘላቂ መፍትሔ አተገባበር ላይ ኢሰመኮ ካከናወናቸው በርካታ ውትወታዎች ዋነኞቹ ናቸው።

ይህ ዓመታዊ ሪፖርት በአራት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን ከዚህ አጠቃላይ መግቢያ በመቀጠል በክፍል አንድ የመረጃ አሰባሰብ ሥነ ዘዴ፣ ኢሰመኮ ክትትል ያከናወነባቸውን ቦታዎች/መጠለያ ጣቢያዎች እና ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ይዘረዝራል። በክፍል ሁለት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን አስመልክቶ የሕግ ማዕቀፍ ትንተና ተደርጓል። በክፍል ሦስት በኢትዮጵያ ስላለው አጠቃላይ የመፈናቀል ሁኔታ፣ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የመብቶች አያያዝ ሁኔታ ጋር ተያይዞ በእመርታነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ተግባራትን እንዲሁም አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችን ይቃኛል። የሪፖርቱ አራተኛ እና የመጨረሻ ክፍል ማጠቃለያ ነጥቦችን እና ምክረ ሐሳቦችን ይዟል።

## የመረጃ አሰባሰብ ሥነ-ዘዴ

ኢሰመኮ በአጠቃላይ ሥራውን የሚያከናውነው ኢትዮጵያ ተቀብላ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን እንዲሁም ብሔራዊ ሕጎችን መሠረት አድርገው በተዘጋጁ የሰብአዊ መብቶች መስፈርቶች እና መለኪያዎች ነው። በዚህ ሪፖርት

ውስጥ የተካተቱ ግኝቶች ኢሰመኮ በራሱ አነሳሽነት እና በቀረቡለት አቤቱታዎች መነሻነት ካደረጋቸው ክትትል እና ምርመራዎች፣ ምክክር መድረኮች እንዲሁም ከመለስተኛ ጥናትና ምርምሮች ከተሰበሰቡ መረጃዎች እና ማስረጃዎች የተውጣጡ ናቸው።

በሪፖርቱ ውስጥ የተካተቱ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለመሰብሰብ ኢሰመኮ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል። ከእነዚህም ውስጥ ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሕጎችን በመተንተን እና የሰብአዊ መብቶች አያያዝ መለኪያ መርሖችን እና ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ የክትትልና የምልከታ ቅጾች እና መጠይቆች ይገኙበታል። በዚህም ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሚደረገውን ሰብአዊ ድጋፍና ጥበቃ፣ የዘላቂ መፍትሔ አተገባበር እንዲሁም አጠቃላይ የሰብአዊ መብቶች አያያዝን በተመለከተ፤ ከተፈናቃዮች፣ ከተፈናቃይ ተወካዮች፣ ከመጠለያ ጣቢያ አስተባባሪዎች፣ ከተፈናቃይ ተመላሾች፣ በየደረጃው ካሉ የክልል እና የፌዴራል የመንግሥት ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በአጠቃላይ 154 ቃለ መጠይቆች፣ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ ተፈናቃይ ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋውያንን እና አካል ጉዳተኞችን እንዲሁም የማይድን/ቋሚ የጤና ችግር ያለባቸውን ተፈናቃዮች ያሳተፉ 78 የቡድን ውይይቶች እና የአካል ምልከታ በማድረግ መረጃና ማስረጃዎች ተሰብስበዋል። የሕግ እና አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ትንተና ተከናውኗል።

ከዚህ በተጨማሪ የክትትልና ምርመራ ግኝቶቹን መሠረት በማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ እና በክልል ከተሞች የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የተለያዩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ውይይቶች ተደርገው ግብአት ተሰብስቧል። ይህ ሪፖርት ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. በሰንጠረዥ ቁጥር 01 በተጠቀሱት አካባቢዎች/ቦታዎች ያለውን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የሚያሳይ ነው። ሆኖም በተጠቀሱት ክልሎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን አጠቃለይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በዝርዝር፣ በብዛትና ዐይነት ሙሉ ለሙሉ የሚያሳይ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም።

## ክትትልና ምርመራ የተከናወነባቸው አካባቢዎች

ኢሰመኮ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች ሁኔታን አስመልክቶ ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በ8 ክልሎች በአጠቃላይ 13 ክትትሎች እና 1 ምርመራ አካሂዷል። ተፈናቃዮች የሚገኙባቸውን 31 የመጠለያና ጊዚያዊ ማቆያ ጣቢያዎችን፣ 13 ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩባቸውን፣ 3 ወደቀድሞ ቀያቸው የተመለሱባቸውን እንዲሁም 3 ወደ ሌላ ቦታ ተዘዋውረው የሚኖሩባቸው አካባቢዎች በክትትል እና ምርመራ ሥራዎች ለመሸፈን ተችሏል። በዚህም በአጠቃላይ የ333,889 ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታን ለመገምገም ተችሏል። ይህም ዓለም አቀፍ የፍልሰት ድርጅት በግንቦት ወር ባወጣው ሪፖርቱ በኢትዮጵያ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቁጥር ብሎ ከጠቀሰው (3.3 ሚሊዮን) ጋር ሲስተያይ 10 በመቶውን (10%) ይሸፍናል። ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ከተገለጹት አካባቢዎች በተጨማሪም በ2015 ዓ.ም. በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በተፈናቃዮች የቤት፣ መሬት እና ሌሎች የንብረት መብቶች ላይ ያደረገውን ምርመራ መሠረት በማድረግ የምክረ ሐሳብ አፈጻጸም ክትትል እንዲሁም ውትወታን አከናውኗል።

**ክትትልና ምርመራ የተከናወነባቸው ቦታዎች**

| ተ.ቁ | ክልል | ዞን/ወረዳ/ከተማ | ተፈናቃዮች የሚገኙበት መጠለያ ጣቢያ/ቦታ | የተፈናቀሉበት ጊዜና ቦታ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አማራ ክልል | ሰሜን ሸዋ ዞን ደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር | ወይንሸት፣ ባቂሎ እና ቻይና ካምፕ መጠለያ ጣቢያዎች | ከ2013 ዓ.ም. ጀምሮ ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ፣ ምዕራብ፣ ሆሮጉድሩ፣ ቄለም ወለጋ እና ምዕራብ ሸዋ ዞኖች የተፈናቀሉ |
| | | ሰሜን ወሎ እና ዋግህምራ ዞን | ቆቦ፣ ወልድያ እና ሰቆጣ ከተሞች | በ2016 ዓ.ም. ከአላማጣ፣ ራያ አላማጣ፣ ኮረም፣ ኦፍላ እና ዛታ |
| 2. | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል | መተከል ዞን ዳንጉር፣ ማንዱራ፣ ድባጤ እና ቡለን ወረዳዎች | ማንቡክ፣ ገነተማርያም፣ ድባጤ መጠለያ ጣቢያዎች | በ2013 ዓ.ም. መተከል ዞን ማንዱራ፣ ድባጤ እና ቡለን ወረዳዎች |
| 3. | ጋምቤላ ክልል | ኑዌር ዞን ጂካዎ ወረዳ፣ | ጂካዎ ከተማ | ነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ከጂካዎ ወረዳ |
| | | አኙዋ ብሔረሰብ ዞን | ጎግ፣ ጆር እና ጋምቤላ ዙሪያ ወረዳዎች፣ | ነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ከጎግ፣ ጆር እና ጋምቤላ ዙሪያ ወረዳዎች፣ |
| | | ጋምቤላ ከተማ አስተዳደር | ጋምቤላ ከተማ | መስከረም 2016 ዓ.ም. ጋምቤላ ከተማ |
| | | አኙዋ ብሔረሰብ ዞን ጆር ወረዳ | ኡንጎጊ ከተማ አሌላ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት | መጋቢት ወር 2016 ዓ.ም. ከጆር ወረዳ ከኡቱዎል 01 እና 02፣ አለሚ፣ ሌሮ፣ ኡራሃ እና ቶው ቀበሌዎች |
| 4. | ሐረሪ ክልል | በሐኪም እና በሸንኮር ወረዳዎች | በሐኪም ወረዳ በሐማሬሳ የተፈናቃዮች መጠለያ እና በሸንኮር ወረዳ፤ የሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ ውስጥ | በ2010 ዓ.ም. ከሶማሊ ክልል እንዲሁም በ2011 ዓ.ም. ከሐረሪ ክልል ከአሚር ኑር ወረዳ ገንደፌሮ ከሚባል አካባቢ የተፈናቀሉ |
| 5. | ኦሮሚያ ክልል | ምሥራቅ ወለጋ ዞን ዋዩ ቱቃ፤ ሲቡ ሲሬ፤ ጎቡ ሰዮ ወረዳዎች፤ | ጂማታ ቀበሌ፤ ሲሬ ከተማ 01፤ ጨፌ ጃለሌ እና ጨሪ ቀበሌዎች፤ አና ከተማ ጊዜያዊ ጣቢያዎች | ከ2013 ዓ.ም. ጀምሮ ከምሥራቅ ወለጋ ዞን ዋዩ ቱቃ፤ ሲቡ ሲሬ፤ ጎቡ ሰዮ ወረዳዎች እና ምዕራብ ወለጋ ጊምቢ እና ጉሊሶ ወረዳዎች |
| | | ምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ እና ጉሊሶ ወረዳዎች | ቶሌ ቀበሌ እና ጉሊሶ ከተማ ግዚያዊ ጣቢያዎች | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ምሥራቅ ሸዋ ዞን ቦራ እና ዱግዳ ወረዳዎች | መቂ፣ አለምጤና፣ ሞጆ፣ ባቱ እና አዳማ ከተሞች | በ2015 ዓ.ም. ከቦራ ወረዳ በርታ ሳሚ (አውራጎዳና)፣ ጂርሜ ቦራ ቀበሌዎች እና ከዱግዳ ወረዳ ጀዌ ቦፎ፣ ኦዳ ፊላ፣ ወዮ ገብርኤል ቀበሌዎች |
| 6. | ትግራይ ክልል | ማእከላዊ ዞን አክሱም እና አድዋ ከተሞች | ቀዳማዊ ምኒልክ እና አክሱም 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣<br>ንግስተ ሳባ መሰናዶ ትምህርት ቤት | በ2013 ዓ.ም. ከቃፍታ ሁመራ፣ ወልቃይት፣ ፀገዴ፣ ማይካድራ፣ ታህታይ ኣዲያቦ፣ ሽራሮ፣ ፀለምቲ፣ ሓውዜን፣ ጋንታ ኣፈሹም፣ ግሎመከዳ፣ ኢሮብ፣ አላማጣ፣ ኮረም፣ ኦፍላ፣ ራያ አላማጣ እና አፋር ክልል |
| | | ምሥራቅ ዞን አዲግራት እና ውቅሮ ከተሞች፤ | ፍኖተ ብርሃን እና ውቅሮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የድሮ አየር መንገድ፣ | |
| | | መቀሌ ኲሓ ክፍለ ከተማ | መቀሌ ጤና ጣቢያ፣ ማይ ወይኒ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | |
| 7. | ሶማሊ ክልል | ፋፈን ዞን | ዱርዋሌ ቀበሌ እና ጎልጀኖ ከተማ | በ2008 ዓ.ም. ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን በልበሊቲ፣ ሀበሮ፣ እና ጉድና፣ ገለምሶ፣ ዳሮ ለቡ ወረዳዎች እና ባሌ ዞን ጊንደር ወረዳ |
| 8. | ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል | ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ | ሲየስ፣ ልበ ሙቀት፣ ደሚች፣ ዶሼ፣ ሀዶ፣ ሰለኝ፣ ነብረሙስ፣ ሽራ፣ ቶሮንጎሌ፣ ኦቾሎች፣ ደለረሌ እና ቡቡአ | ከ2012 ዓ.ም. ጀምሮ ከደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ |
| | | ደቡብ ኦሞ ዞን ደቡብ አሪ ወረዳ | ቶልታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ጋዘር ከተማ ፖሊስ ጣቢያ፣ ጂንካ ከተማ | በመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም. ከደቡብ አሪ ወረዳ ቶልታ፣ ሜፀር፣ ጋዘር እና በርካ ቀበሌዎች፣ ሰሜን አሪ ወረዳ ሸንጋማ ቢል ቀበሌ እና ምባ አሪ ወረዳ ዉባመር እና ባላመር ቀበሌዎች። |

# ተግዳሮቶች

በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች በነበረው የጸጥታ ችግር እና የደኅንነት ሥጋት እንዲሁም ኢሰመኮ ካለው የሰው ኃይል እና የሎጀስቲክ ውስንነት ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው ቦታዎች ሁሉ በሚፈለገው ፍጥነት እና መጠን ተገኝቶ ክትትል እና ምርመራ ለማከናወን አልተቻለም። በዚህም በሀገራችን ያለውን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሙሉ ምስል በዚህ ሪፖርት ማቅረብ አልተቻለም። በተለይም በአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች ተባብሶ በቀጠለው ግጭት ምክንያት በተሽከርካሪ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መንቀሳቀስ አስቸጋሪ በመሆኑ፣ በተለያዩ መጠለያ ጣቢያዎች እና ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው በሚኖሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ በሚፈለገው መጠን ክትትል እና ምርመራ ማድረግ አልተቻለም። ከዚህም ሌላ በክትትልና ምርመራ የተለዩ ክፍተቶችን ለመቅረፍ በኢሰመኮ የሚሰጡ ምክረ ሐሳቦችን የመንግሥት እና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ፈጣን እና ቀልጣፋ ምላሽ አለመስጠት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ በሚፈለገው ደረጃ እንዳይሻሻል አድርጓል።



Photo credit: EHRC/Media and Comms/Haleluya Abebe

WWW.EHRC.ORG



Photo credit: EHRC/Media and Comms/ Israel Solomon

# ክፍል ፪

# ክፍል ሁለት

## የሕግ ማዕቀፍ

በዓለም አቀፍ ደረጃ በልዩ ሁኔታ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የተመለከተ የተሟላ እና አስገዳጅነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ባይኖርም፣ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች (Human Rights Treaties)[1]፤ በትጥቅ ግጭት ዐውድ የሰብአዊነት ሕጎች (International Humanitarian Laws)[2] እንዲሁም ሀገራዊ ሰብአዊ መብቶችን የተመለከቱ የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች እና ሕጎች የተፈናቃዮችን ሰብአዊ መብቶች ለመጠበቅ ተግባራዊ ይደረጋሉ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ. በ1998 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) ለአባል ሀገራት እና ሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት ለተፈናቃዮች ተገቢውን ጥበቃ እና ድጋፍ ለማድረግ እንዲቻል የሀገር ውስጥ መፈናቀል መመሪያ መርሖችን በማውጣት በሥራ ላይ አውሏል።[3] መመሪያው በዋናነት በሕይወት የመኖር፣ አካላዊ ደኅንነት፣ ኢ-ሰብአዊ ከሆነ አያያዝ የመጠበቅ፣ ከጾታዊ ጥቃት የመጠበቅ፣ ከመፈናቀል የመጠበቅ፣ የሰብአዊ ድጋፍ የማግኘት፣ የንብረት፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንዲሁም የሲቪልና ፖለቲካ መብቶችን አካቷል። በተጨማሪም መመሪያው በሀገር ውስጥም ይሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ የተፈናቃዮችን መብቶች ለማስከበር የተቋቋሙ አካላት ሊተገብሯቸው የሚገቡ መርሖችን በዝርዝር አስቀምጧል። በዚህ መመሪያ የተካተቱት መርሖች አስገዳጅ የሆኑትን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እና የሰብአዊነት ሕጎች መርሖችን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ በመሆናቸው በአባል ሀገራቱ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አግኝተዋል።

በአህጉር ደረጃ የአፍሪካ ኅብረት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ያሉበትን ከባድ እና ውስብስብ ሁኔታ በመገንዘብ እንዲሁም በተለየ ሁኔታ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ መሆናቸውን በመረዳት በአፍሪካ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍን አስመልክቶ የተደረገ የአፍሪካ ኅብረት ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት-Kampala Convention) ተብሎ የሚታወቀውን እ.ኤ.አ. በ2009 አጽድቋል።[4] ስምምነቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀል መመሪያ መርሖችን፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን እና የሰብአዊነት ሕጎችን መሠረት አድርጎ የወጣ አህጉር አቀፍ ስምምነት ነው። ስምምነቱ በዋናነት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን ለመከላከልና ለማስተዳደር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ እና አደረጃጀት እንዲኖር ያለመ ነው። ኢትዮጵያም ይህንን ስምምነት በ2012 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 1187/2012 አጽድቃ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9 መሠረት የሀገሪቱ የሕግ አካል አድርጋለች።[5] በሀገር አቀፍ ደረጃ ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ ብሔራዊ የሕግ ማዕቀፍ እና ተቋማዊ

---

[1] ለምሳሌ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (1966) ፤ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን (1966) ፤ የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች ቻርተር (1981) ይመልከቱ

[2] The Four Geneva Conventions on International Humanitarian Law (Geneva Conventions I, II, III, IV) and Additional Protocols (P rotocol I, II, III) ይመልከቱ

[3] UN High Commissioner for Refugees (UNHCR), *Guiding Principles on Internal Displacement*, 22 July 1998, ADM 1.1, PRL 12.1, PR00 /98/

[4] African Union, African Union Convention for the Protection and Assistance of Internally Displaced Persons in Africa (Kampala Convention), October 23, 2009.

[5] በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ለመጠበቅ እና ድጋፍ የማድረግ የአፍሪካ ኅብረት ስምምነትን የካምፓላ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 1187/2012 ፣ 2012 ዓ.ም.

አደረጃጀት እንዲኖር የሚያስገድድ በመሆኑ ይህን ለማድረግ የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

በካምፓላ ስምምነት በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ማለት “በተለይ በትጥቅ ግጭት፣ አጠቃላይ ጥቃት በሚፈጸምባቸው ሁኔታዎች፣ በሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ወይም በሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት፣ ወይም እነዚህ ሁነቶች የሚያስከትሏቸውን ውጤቶች ለመከላከል ከቤታቸው ወይም ከመደበኛ የመኖሪያ ቦታቸው እንዲሸሹ ወይም ለቀው እንዲሰደዱ የተገደዱ ነገር ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያለውን የሀገር ድንበር ያልተሻገሩ ሰዎች ወይም የሰዎች ስብስብ ናቸው”[6]። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያወጣው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መመሪያ መርሖች (UN Guiding Principles on Internal Displacement) ሥርም ተመሳሳይ ትርጓሜ ተቀምጧል[7]። በተጨማሪም እ.ኤ.አ. በ2006 የወጣው ቀጠናዊ የግሬት ሌክስ ፕሮቶኮል (Great Lakes Protocol) ላይ የተጠቀሰው ትርጉምም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው[8]።

በካምፓላ ስምምነት መሠረት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ያለምንም ዐይነት መድልዎ ጥበቃና ድጋፍ የማድረግ ግዴታ እና ኃላፊነት በዋነኝነት በመንግሥታት ላይ የተጣለ ነው[9]። መንግሥት ሰዎች እንዳይፈናቀሉ ተገቢውን የመከላከል እርምጃዎች የመውሰድ እንዲሁም በመፈናቀል ወቅት እና በኋላም የተፈናቃዮችን መብቶች የማስጠበቅ እና የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽ እንዲሆን የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ግዴታ አለበት። በዚህም መንግሥት በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ለሚገኙ ተፈናቃዮች ያለ ምንም መድሎ ደኅንነታቸውን የማስጠበቅ፣ ወቅታዊ፣ በቂና ያልተቆራረጠ የሰብአዊ ድጋፍ የማቅረብ ዋነኛ ግዴታዎች ተጥሎበታል። በተለይም መንግሥት ለተፈናቃዮች ምግብ፣ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ፣ መጠለያ፣ የሕክምና፣ ትምህርት እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን የማቅረብ ግዴታ አለበት። የሚያደርገውን የሰብአዊ ድጋፍ በራሱ ዐቅም ማቅረብ ሳይችል ሲቀር ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና የሰብአዊ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፣ ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና ከሌሎች መሰል ተቋማት ድጋፍ በማሰባሰብና በማስተባበር ግዴታውን መወጣት ይጠበቅበታል። እነዚህ ድጋፎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተቀባይ ማኅበረሰብንም ያማከሉ መሆን አለባቸው[10]።

መፈናቀል በተከሰተ ጊዜ መንግሥት በልዩ ትኩረት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በጾታ፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት እንዲሁም በጤንነት ሁኔታ የተሰባጠረ ሙሉ መረጃ የያዘ መዝገብ ማደራጀት እና በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ ይኖርበታል። መንግሥት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶቻቸውን መጠየቅ እና መተግበር እንዲችሉ የሚያስፈልጓቸውን እንደ ፓስፖርት፣ የግል መታወቂያ ሰነዶች፣ የሲቪል የምስክር ወረቀቶች፣ የልደት የምስክር ወረቀቶች እና የጋብቻ የምስክር ወረቀቶች የመሳሰሉ ሰነዶችን እንዲያገኙ የማድረግ ግዴታ አለበት[11]። ተፈናቃዮች እነዚህን ሰነዶችን ለማግኘት ሲሉ ወደ ቀድሞ የመኖሪያ ቦታቸው እንዲመለሱ ያለመገደድ መብት ያላቸው በመሆኑ መንግሥት ምክንያታዊ ያልሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ሳያስቀምጥ

---

[6] በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ለመጠበቅ እና ድጋፍ የማድረግ የአፍሪካ ኅብረት ስምምነትን የካምፓላ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 1187/2012 ፣ አን ቀ ጽ 3 (2) (ሀ)

[7] UN Guiding Principles on Internal Displacement, Introduction, Scope and Purpose, No.2

[8] Regional Treaties, Agreements, Declarations and Related, Protocol on the Protection and Assistance to Internally Displaced Persons, November 30,2006, Art 1 (4)

[9] የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 5 (1)

[10] የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 (2) (3)

[11] የካምፓላ ስምምነት፣ አንቀጽ 13

አዲስ ሰነዶችን እንዲያገኙ እንዲሁም በመፈናቀል ሂደት የጠፉ ወይም የተበላሹ ሰነዶቻቸው እንዲተኩላቸው ባሉበት ቦታ ሁኔታዎችን ሊያመቻችላቸው ይገባል።

መንግሥት ለተፈናቃዮች ያለምንም ዐይነት መድልዎ ጥበቃ የማድረግ እና አጥጋቢ በሆነ ደኅንነት፣ ሰብአዊ ክብር እና ከማናቸውም የጸጥታ እና ደኅንነት ሥጋት ነጻ ሆነው እንዲኖሩ ለማስቻል አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ አለበት[12]። የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ደኅንነት ለማስከበር ወይም የሕዝብ ጸጥታ፣ ደኅንነት እና ጤና ለማስጠበቅ አስፈላጊ፣ ምክንያታዊና ተመጣጣኝ ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ የተፈናቃዮችን ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ እንዲሁም የመኖሪያ ቦታቸውን የመምረጥ ነጻነታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት በመንግሥት ላይ ተጥሏል[13]። በተመሳሳይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ከዘፈቀደ እሥራት ወይም የመንቀሳቀስ ነጻነት ገደብ፣ ማንኛውንም ዐይነት ወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃትን ጨምሮ ከጭካኔ እና ከማሰቃየት ተግባርና ሌሎች ደኅንነታቸውን አደጋ ላይ ከሚጥሉ መሰል ድርጊቶች የመጠበቅ መብት አላቸው[14]። መንግሥት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የተጠለሉባቸውን ቦታዎች የሲቪልና የሰብአዊነት ባሕርያት የማክበር እና የማስጠበቅ እንዲሁም የታጠቁ ቡድኖች ወደ እነዚህ ቦታዎች ሰርገው በመግባት ጉዳት እንዳያደርሱ የመከላከል እና እንደዚህ ዐይነቶቹን ቡድኖች ትጥቅ የማስፈታት ግዴታ ተጥሎበታል[15]።

ሌላው በመንግሥት ላይ የተጣለው ግዴታ ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለሆኑት ከቤተሰቦቻቸው የተለዩ እና ብቻቸውን ያሉ ሕፃናት፣ እማወራዎች፣ ነፍሰ ጡር ሴቶች፣ ጨቅላ ሕፃናት ያላቸው እናቶች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች ወይም የማይድን/ቋሚ የጤና ችግር ያለባቸውን ጨምሮ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች ልዩ ጥበቃና ድጋፍ ማድረግ ነው[16]። በተመሳሳይ መንግሥት፤ ለሴት ተፈናቃዮች የሥነ ተዋልዶና የሥርዓተ ጾታ ጤና አገልግሎትን እንዲሁም ወሲባዊ እና ሌሎች ተያያዥ ጥቃቶች ለደረሰባቸው ተፈናቃዮች ተገቢውን የሥነ ልቦና እና የማኅበራዊ ድጋፍ ለመስጠት እና ጥበቃ ለማድረግ ልዩ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል[17]። በተጨማሪ መንግሥት ለተፈናቃዮች ድጋፍና ጥበቃ ለማድረግ በተያዙ ዕቅዶችና ውሳኔዎች ላይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ትርጉም ባለው ሁኔታ ማሳተፍ አለበት[18]።

የካምፓላ ስምምነት ከመንግሥት ሌላ በግጭት ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ላይም ግዴታዎችን ያስቀመጠ ሲሆን በግጭት ተሳታፊ የሆኑ የታጠቁ ኃይሎች በዘፈቀደ ወይም በኃይል ከማፈናቀል፣ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሚደረግ የሰብአዊ ጥበቃ እና ድጋፍን ከማስተጓጎል፣ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ መብትን ከመገደብ፤ ተፈናቃዮችን ከመሰወር እና ከማገት፤ በኃይል ለውትድርና ከመመልመል፤ ክብርና ደኅንነታቸውን አደጋ ላይ ከሚጥሉ እንዲሁም ሌሎች ሰብአዊ መብቶችን ከሚጥሱ ድርጊቶች እንዲቆጠቡ ክልከላዎችን ያስቀምጣል። በተመሳሳይ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና የሰብአዊ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ለተፈናቃዮች ጥበቃና ድጋፍ በሚያቀርቡበት ወቅት መብቶቻቸውን እንዲያከብሩ

12 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9(2)(ሀ)
13 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 (2) (ረ)
14 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 (1) (ሐ) እና (መ)
15 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 (2) (ሰ)
16 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 (2) (ሐ)
17 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 (2) (ሐ) እና (መ)
18 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 (2) (ተ)

እና ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅትም አግባብነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ መለኪያዎችን እና የሥነ ምግባር መርሖችን መሠረት አድርገው መሆን እንዳለበት ተመላክቷል[19]፡፡

በመፈናቀል ጊዜ ከሚደረገው ጥበቃና ድጋፍ በተጨማሪ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የዘላቂ መፍትሔ አማራጮች ሊመቻቹላቸው ይገባል፡፡ በዚህም መንግሥት ደኅንነትንና ክብርን በጠበቀ መልኩ በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የመመለስ (Voluntary Return)፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ተዋሕዶ የመኖር (Local Integration) ወይም ወደ ሌላ ቦታ የመስፈር (Relocation) መፍትሔዎችን በማመቻቸት እና አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር ለመፈናቀል ችግር ዘላቂ መፍትሔዎችን የማፈላለግ ግዴታ ተጥሎበታል[20]፡፡ የዘላቂ መፍትሔ አማራጮች ሲተገበሩም ተፈናቃዮች በነጻ ፈቃዳቸውና በመረጃ ተደግፈው መምረጥ እንዲችሉ፤ ስለ አማራጮቹ ሐሳባቸውን ሊጠየቁና ፈቃዳቸውን ሊሰጡ፤ እንዲሁም ዘላቂ መፍትሔዎችን በማመቻቸት ሂደትና ውሳኔ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ሊደረግ ይገባል[21]፡፡

መንግሥት ዘላቂ መፍትሔ ለመፈለግ በሚያደርገው ጥረትም ሆነ በሌላ አኳኋን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ደኅነታቸውን፣ ነጻነታቸውን እና/ወይም ጤናቸውን አደጋ ላይ ወደሚጥል ማንኛውም ቦታ በኃይል ያለመመለስ ወይም እንዲሰፍሩ ያለመገደድ መብታቸው መከበሩን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት[22]፡፡ ከዚህም ሌላ መንግሥት ተፈናቃዮች በዘላቂነት በሚቋቋሙበት አካባቢ የማኅበራዊ አገልግሎቶች እና መሠረተ ልማቶች አስቀድመው መሟላታቸውን፤ የቤት፤ መሬት እና ንብረት ይዞታዎች መከበራቸውን እንዲሁም ለወደመ ሀብት እና ንብረት ካሳ መከፈሉን ወይም ምትክ መሰጠቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት፤ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች እንዳይደርሱ የመከላከል እና አደጋዎች በሚደርሱበት ጊዜም ለተጎጂዎች አስፈላጊው እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ የማድረግ ኃላፊነትን በመንግሥት ላይ ግዴታ ይጥላል[23]፡፡ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው ያለምንም አድልዎ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ለሁሉም ዜጎች ተፈጻሚ በሆኑት መብቶች እንዲሁም በመንግሥት በጀት በሚተገበሩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች እኩል ተጠቃሚነት መብት አላቸው፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ንብረት የማፍራት፣ በንብረቱ የመጠቀም፣ የንብረቱን የባለቤትነት ወይም የመጠቀም መብት በሕጋዊ መንገድ የማስተላለፍ መብት አለው[24]፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አርሶ አደር የእርሻ መሬት ባለይዞታ የመሆንና ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ያለው መሆኑም በሕገ መንግሥቱ በግልጽ ተደንግጓል[25]፡፡ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችም የዚህ መብት ባለቤት በመሆናቸው በመፈናቀል ወቅት ትተውት የሄዱትን የግልም ይሁን የጋራ ንብረት የመጠበቅ፣ አላግባብ እና ሕገወጥ በሆነ መልኩ ይዞታቸው ያለመወረስ መብታቸውን ማክበር እና ማስከበር የመንግሥት ግዴታ ነው[26]፡፡ ተፈናቃዮች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ቀድሞ የመኖሪያ አካባቢያቸው መመለስ አለመቻላቸው፤ በመፈናቀላቸው ምክንያት ጥለውት የሄዱትን ቤት፣ መሬት እና ሌሎች

---

19 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 6 እና 7 (5)
20 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 11 (1)
21 የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 11 (2)
22 የካምፓላ ስምምነት አንቀፅ 9 (2) (ሠ)
23 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴምክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥስት፣ አንቀጽ 89 (3)
24 በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 (1)
25 በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 (4)
26 የተባበሩት መንግሥታት የሀገር ውስጥ መፈናቀል የመመርያ መርሖዎች መርሕ 21(3)

ንብረቶችን መልሶ የማግኘት መብት የማያሳጣቸው በመሆኑ በመፈናቀላቸው ምክንያት ጥለውት የሄዱትን ንብረት መልሶ እንዲያገኙና ይዞታቸው እንዲከበር ድጋፍ የማድረግ እና ሁኔታዎችን የማመቻቸት ኃላፊነት የመንግሥት ነው።

በአጠቃላይ መንግሥት ሰዎችን ሊያፈናቅሉ ከሚችሉ ሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ጉዳት ሳይደርስ አስቀድሞ የመከላከል፣ መፈናቀል በተከሰተ ጊዜም በእያንዳንዱ ሂደት ለተፈናቃዮች መብቶች አጠባበቅ አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ እና በዘላቂነት መልሶ የማቋቋም ግዴታ ተጥሎበታል።



Photo credit: EHRC/Media and Comms/Israel Solomon

WWW.EHRC.ORG



Photo credit: EHRC/Media and Comms/ Israel Solomon

# ክፍል ፫

# ክፍል ሦስት

## በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የመፈናቀል ሁኔታ፣ ቁልፍ እመርታዎች እና አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች

### አጠቃላይ የመፈናቀል ሁኔታ መረጃ

ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ መጠነ ሰፊ የሆነ የሀገር ውስጥ መፈናቃል የተከሰተ ሲሆን ይህ ሪፖርት በሸፈነው ከሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሰኔ ወር 2016 ዓ.ም. ወቅትም ችግሩ አሳሳቢ ሆኖ ቀጥሏል። በየጊዜው በሚከሰቱ ማንነትን መሠረት ያደረጉ የታጠቁ ቡድኖች ጥቃቶች፣ በመንግሥት እና በታጠቁ ቡድኖች መካከል በሚደረጉ ግጭቶች እና ዘላቂ ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ መፍትሔ ባልተሰጠባቸው የወሰን ይገባኛል ጥያቄዎች ምክንያት በሚከሰት ግጭት እና ጦርነት፣ እንዲሁም በተፈጥሮ አደጋ፣ በአየር ንብረት ለውጥ እና ሌሎች ምክንያቶች በአፋር፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሐረሪ፣ ኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ ሶማሊ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልሎች ተፈናቅለው እርዳታ ጠባቂ የሆኑ በየመጠለያ ጣቢያው እና ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ይገኛሉ።

እንደ ዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት (International Organization for Migration—IOM) መረጃ በኢትዮጵያ ከ3.3 ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 2.2 ሚሊዮን (68.7 ከመቶ) የሚሆኑት በግጭትና ጦርነት፣ 0.5 ሚሊዮን (16.8 ከመቶ) የሚሆነት በድርቅ ቀሪዎች ደግሞ በሌሎች ምክንያቶች በተለይም ከአየር ንብረት ለውጥ እና በልማት ሥራዎች የተፈናቀሉ ናቸው[27]። ከእነዚህም ውስጥ 56 ከመቶ የሚሆኑት ከ1 ዓመት፣ 23 ከመቶ የሚሆኑት ከ2 እስከ 4 ዓመት እና 11 ከመቶ የሚሆኑት ከ5 ዓመት በላይ በተራዘመ የመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ።[28] ይህ አኃዝ በአማራ ክልል ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት መረጃ በበቂ ሁኔታ ያልተሰበሰበ በመሆኑ ቁጥሩ ከዚህም በላይ ክፍ ሊል እንደሚችል ይጠበቃል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መፈናቀል አብዛኛው በግጭት ምክንያት በመሆኑ በመፈናቀል እና በድኅረ መፈናቀል ወቅት ሰዎች ለተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሲጋለጡ በስፋት ይስተዋላል። ይህም ሰዎች የመኖሪያ ቀያቸውን ለቀው እንዲሸሹ፣ ንብረታቸው እንዲወድምና እንዲዘረፍ ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር ቀዳሚ የሆነውን የሰዎች በሕይወት የመኖር መብትን ጨምሮ አጠቃላይ ሀገራዊ ሰላምና ደኅንነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። በኃይል ማፈናቀል በርካታ ሰብአዊ እና ቁሳዊ ጥፋትን የሚያስከትል በመሆኑ ነዋሪዎች ሕይወታቸውን ለማትረፍ ቤተሰቦቻቸውን ይዘው እንዲሸሹ እና ወደ ሌላ አካባቢ ሄደው ጥገኝነት እና ድጋፍ እንዲጠይቁ ያስገድዳቸዋል። ይህም ተፈናቃዮችን ሞትን ጨምሮ ለተለያዩ አካላዊ ጉዳት

---

[27] IOM, Ethiopia National Displacement, Site Assessement Round 35 and Village Assessement Survey Round 19, Report 19 (November — May 2024) https://dtm.iom.int/reports/ethiopia-national-displacement-report-19-november-2023-may-2024?close=true

[28] UNOCHA, Internal Displacement Overview, https://reliefweb.int/report/ethiopia/ethiopia-internal-displacement-overview-june-2024

የሚዳርግ፣ ያፈሩትን ንብረት እና የገቢ ምንጫቸውን የሚያሳጣ በመሆኑ መሠረታዊ የሆኑትን በሕይወት የመኖር፣ አካላዊ ደኅንነት እና ንብረት የማፍራት መብቶችን እንዲጣሱ ከማድረግ ባለፈ ለተለያዩ ማኅበራዊ እና ሥነ ልቦናዊ ቀውሶች ዳርጓቸዋል። በመፈናቀል ወቅት የሚደረገው ጥበቃ እና ድጋፍ ወቅቱን ያልጠበቀ፣ በቂ እና ተከታታይነት እንዲሁም አካታችነት የሚጎድለው መሆኑ ሁኔታውን የበለጠ ያባብሰዋል። በዚህ ምክንያት ተፈናቃዮች ራሳቸውን እና ቤተሰብን ለመደገፍ ሲሉ አሉታዊ ውጤቶች ያሏቸውን አማራጮች (negative coping mechanisms) ለመውሰድ ይገደዳሉ። ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና የማይድን/ቋሚ የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች ለተደራራቢ የመብት ጥሰት ተጋላጭ በመሆናቸው በመፈናቀል አውድ ውስጥ ለከፋ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ይዳረጋሉ።

በተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በአማራ፣ ኦሮሚያ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ያለው የጸጥታ ችግር አሁንም ሰዎችን ከማፈናቀል ባለፈ ለተፈናቃዮች ሰብአዊ ድጋፍ እና ጥበቃ ለማድረግ አስቸጋሪ አድርጎታል። በተለይም ለነፍስ አድን የሚሆን ምግብና መድኃኒቶችን ለተፈናቃዮች ለማድረስ እንዲሁም ለሕክምና ከቦታ ቦታ ለሚንቀሳቀሱ ተፈናቃዮች ትልቅ ፈተና ሆኗል። በዚህም ሳቢያ ተፈናቃዮች ሊደረግላቸው የሚገባውን ድጋፍ እና ጥበቃ እያገኙ አይደለም። በጸጥታ ችግሩ ላይ በሀገሪቱ ያለው የመሠረታዊ ፍጆታዎች ዋጋ ንረት እና የተፈጥሮ አደጋ ተዳምሮ የመጠለያ፣ የጤና እና የትምህርት አገልግሎት፣ የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች እጥረት በተለይም በመጠለያ ጣቢያዎች በሰፊው ይስተዋላል። ይህ ችግር በተለይ ደግሞ ልዩ ድጋፍ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ በጣም የከፋ ነው።

የተፈናቃዮችን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘቡ በመንግሥት አካላት የሚወሰኑ ሕጋዊ፣ አስፈላጊ እና ተመጣጣኝ ያልሆኑ የተለያዩ ውሳኔዎች መብቶቻቸውን በማጣበብ ሁኔታውን ሲያባብሱ ይስተዋላል። በተለይ ተፈናቃዮች ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ አግኝተው፣ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ሠርተው እራሳቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን ማስተዳደር አለመቻል እንዲሁም በተራዘመ የመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ ድጋፍ ጠባቂ ሆነው መቆየታቸው፤ ተፈናቃዮች እራሳቸውን ችለው ወደ ቀድሞ ሕይወታቸው በዘላቂነት እንዳይመለሱ ከማድረጉም በላይ በተቀባይ ማኅበረሰብ እና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው።

ለተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ የማፈላለግ ሂደቱ ተፈናቃዮችን በአግባቡ እና ትርጉም ባለው ሁኔታ ያሳተፈ እንዲሁም ሰብአዊ ክብራቸውን እና ደኅንነታቸውን በጠበቀ መልኩ ባለመከናወኑ ለተደጋጋሚ መፈናቀል (recurrent displacement) ሲዳርጋቸው በስፋት ይስተዋላል። መንግሥት ተፈናቃዮችን በመመለስ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት ዕቅድ ቢኖረውም ተፈናቃዮች ቀድሞ ይኖሩባቸው በነበሩ አካባቢዎች ያለው የጸጥታ ችግር ባለመቀረፉ እና የደኅንነት ሥጋት በመኖሩ ተፈናቃዮችን በመመለስ ዘላቂ መፍትሔ የመስጠት አማራጭ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ከጸጥታ ችግሩ ባለፈ የተፈናቃዮች የቤት፣ የመሬት እና የንብረት መብቶች አተገባበር ላይ ሰፊ ክፍተቶች በመኖራቸው፣ የወደሙ መኖሪያ ቤቶች ባለመሠራታቸው እና መሠረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽ ባለመሆናቸው በተለያዩ ክልሎች የተጀመሩ የዘላቂ መፍትሔ ፕሮግራሞች በሚፈለገው መጠን ውጤታማ መሆን አልቻሉም። ከዚህም ሌላ ተፈናቃዮች በዘላቂነት ተቋቁመውና ገቢ አግኝተው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት አስቻይ ሁኔታ ላይ እስኪደርሱ ሰብአዊ ድጋፍ እንዲሁም በተሟላ ሁኔታ የማኅበራዊ አገልግሎት አለማግኘታቸው እንዲሁም ለደረሰባቸው የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተገቢውን ፍትሕ እና ካሳ የሚያገኙበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ በአሳሳቢነት የሚጠቀስ ነው።

# ቁልፍ እመርታዎች

- መጋቢት ወር 2016 ዓ.ም. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጸደቀው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የእውነት ማውጣት ሂደቱ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ሌሎች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ባካተተ መልኩ እንደሚተገበር እንደ አንድ የፖሊሲ አቅጣጫ መቀመጡ፣ እና ከሽግግር ፍትሕ ሥርዓት አተገባበር ጋረ በተያያዘ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሽግግር ፍትሕ ሂደት ውስጥ በአግባቡ መስተናገዳቸውን፣ ወደ ቦታቸው መመለሳቸውን እና መሰል መብቶች የተጠበቁላቸው ስለመሆኑ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ የሰላም ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት መሆኑን በግልጽ መቀመጡ፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ የሀገር ውስጥ መፈናቀልን ከመከላከል አንስቶ ዘላቂ መፍትሔ እስከ መስጠት ያሉ ተግባራትን ለማከናወን ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ እና ተቋማዊ አደረጃጀት መኖሩ አስፈላጊ እንደሆነ በመገንዘብ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ወር 2012 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 1187/2012 ያጸደቀውን የካምፓላ ስምምነት ማስፈጸሚያ ብሔራዊ ሕግ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት መቅረቡ፤
- ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው አንዳንድ መጠለያ ጣቢያዎች እና ማቆያ ስፍራዎች በተቀባይ ማኅበረሰብ፣ በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት እና በተራድዖ ድርጅቶች የሰብአዊ ድጋፍ በተለይም የምግብና መጠለያ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ድጋፍ ለማቅረብ የሚደረግ ጥረት፣ እንዲሁም በተወሰኑ የተፈናቃይ መጠለያ ጣቢያዎች በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግ የተሰባጠረ የተፈናቃዮች ምዝገባ እና የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መኖሩ፣
- በሶማሊ ክልል በተራዘመ የመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በክልሉ የተለያዩ ቦታዎች በማስፈር ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት በክልሉ መንግሥት እና አጋር ድርጅቶች ትብብር የተጀመሩት አበረታች ሥራዎች መኖራቸው፤
- በብሔራዊ ደረጃ በተጀመረው የዲጅታል መታወቂያ መርኃ ግብር የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሠራር መፈጠሩ፤
- ተቋርጦ የነበረው የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) እና የዓለም የምግብ ፕሮግራም (WFP) የምግብ ድጋፍ መልሶ እንዲጀመር መደረጉ፤[29]
- የኢሰመኮን የክትትል ግኝቶችና ምክረ ሐሳቦች ተቀብለው የተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለማሻሻል አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጡ የወረዳ፣ ክልል እንዲሁም የፌዴራል አመራርና ተቋማት መኖራቸው ለምሳሌ፦
    - በሐረሪ ክልል ሐኪም ወረዳ በሐማሬሳ የተፈናቃዮች መጠለያ እንዲሁም በሸንኮር ወረዳ፣ በሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታዎችን ለማሻሻል፦
    - ለተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔን ለማመቻቸት የመልሶ ማቋቋም ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራ መጀመሩ እና ሂደቱን ለማሳለጥ የሚረዳ ዕቅድ በኮሚቴው መዘጋጀቱ፤
    - በሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ሳያገኙ ከመጠለያው ለማስወጣት እየተደረገ የነበረውን እንቅስቃሴ በማስቆም የተፈናቃዮችን መረጃ የማጥራት ሥራ መሠራቱ፤

---

[29] EHRC Press Statement, https://ehrc.org/ehrc-welcomes-usaids-and-wfps-decision-to-resume-food-assistance-across-ethiopia/

- ○ በሐማሬሳ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ ተጠልለው ይኖሩ ለነበሩ 27 ቤተሰቦች በየወረዳቸው የቀበሌ ቤት መሰጠቱ እንዲሁም ለተቀሩት ተፈናቃዮችም የቀበሌ ቤት የሚያገኙበት ሁኔታ እየተመቻቸላቸው መሆኑ፣ በተመሳሳይ በሸንኮር ወረዳ በሚገኘው የሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ ለሚገኙ ተፈናቃዮች በቀድሞ ቀያቸው የወደሙባቸው ቤቶች ግንባታ እየተካሄደ መሆኑ፤
- ○ በተመሳሳይ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከካፋ ዞን ዴቻ ወረዳ የተፈናቀሉ 63 ቤተሰቦች በመፈናቀል ወቅት ያጡትን የመሬት ይዞታ እንዲያገኙ በሕገ ወጥ መንገድ የተያዙ ቦታዎችን የማስለቀቅ፣ ያልተያዙ መሬቶችን የመለየት እና መሬታቸው ለልማት ሥራ ለተወሰደባቸው ተፈናቃዮች ተለዋጭ መሬት የማዘጋጀት ሥራዎችን ማከናወኑ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የንብረት መብት ተግባራዊ እንዲያደርጉ አስቻይ ሁኔታዎችን የሚፈጥር መሆኑ፤ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ለማሻሻል እና ዘላቂ መፍትሔ ለመፈለግ በክልሉ የተለያዩ አዎንታዊ እርምጃዎች የተወሰዱ መሆኑ በ2016 በጀት ዓመትም ከታዩ መልካም እመርታዎች መካከል ናቸው::

# ዋና ዋና አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች

## ግልጽ የሕግ ማዕቀፍ እና ተቋማዊ አደረጃጀት

ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የተሟላ ጥበቃና ድጋፍ በማድረግ ሰብአዊ መብቶቻቸው መከበራቸውን ማረጋገጥ የሁሉንም መንግሥታዊ ተቋማት ቅንጅት እና ትብብር (collaboration) የሚፈልግ ነው:: የሚመለከታቸውን ተቋማት ተግባራት እና በዘርፉ የተሰማሩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን ሥራዎች ለማስተባበር እና ለመምራት የሚያስችል አሠራር እንዲሁም በሕግ ግልጽ ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት ተቋም አለመኖሩ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሚደረገው ጥበቃ እና ድጋፍ ላይ የአሠራር ክፍተት እንዲኖር ካደረጉ ምክንያቶች መካከል ዋነኛው ነው:: ለተፈናቃዮች የሚደረገውን ድጋፍ እና ጥበቃ ለማቀድ፣ ለመተግበር፣ ለመከታተል እና ለመገምገም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት፣ ተቋማዊ አደረጃጀት እና ኃላፊነት ባለመኖሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ በሚፈለገው ደረጃ መሻሻል አላሳየም::

ለተፈናቃዮች የሚደረጉ የድጋፍና ጥበቃ ሥራዎችን የትኛው የመንግሥት ተቋም በበላይነት የመምራት እና የማስተባበር ኃላፊነት እንዳለበት አለመታወቁ ሥራዎች በተቀናጀ ሁኔታ እና በአግባቡ እንዳይከናወኑ አድርጓል:: በክልል እና ፌዴራል መንግሥት ተቋማት መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሠራርም ግልጽነት የጎደለው በመሆኑ ኃላፊነትን በመወጣት እና ተጠያቂነት በማረጋገጥ ረገድም ውስንነቶች ይታያሉ:: ከዚህም ሌላ የተፈናቃዮችን ጉዳይ በበላይነት ለመምራትና ለማስተባበር መረጃ በወቅቱ መዝግቦ፤ ለፖሊሲ፣ ለዕቅድ እና መረኃ ግብር ዝግጅትና ትግበራ እንዲሁም ለበጀት ውሳኔ በግብአትነት ከመጠቀም አንጻር ክፍተቶች በመኖራቸው ለተፈናቃዮች በቂ የሆነ ጥበቃ እና ድጋፍ እንዳይደረግ እንዲሁም የዘላቂ መፍትሔ አተገባበርም ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል::

የካምፓላ ስምምነት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተገቢው ጥበቃ እና ድጋፍ እንዲደረግላቸው እና ሰብአዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩላቸው የሚያስገድዱ ድንጋጌዎችን በውስጡ የያዘ ቢሆንም፣ በአንቀጽ 3 (2) ሀ መሠረት በስምምነቱ ውስጥ የተደነገጉትን ግዴታዎች የሚያካትትና ስምምነቱን ለማስፈጸም ብሔራዊ ሕግ ጸድቆ ተግባራዊ ባለመደረጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን መብቶች ማስከበር እና ተገቢውን ጥበቃ ማድረግ አልተቻለም:: ከዚህም

ሌላ የሚያፈናቅሉትን እና ጉዳት የሚያደርሱትን በሕግ ተጠያቂ የሚያደርግ እና ተጎጂዎችን ለመካስ የሚያስችል የተደራጀ የአሠራር ሥርዓት ባለመኖሩ ተፈናቃዮች ተገቢውን ፍትሕ ማግኘት አልቻሉም፡፡

## የምዝገባ፣ ሰነድ የማግኘት እና የመንቀሳቀስ መብቶች

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ምዝገባ፣ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የተለያዩ ሰነዶችን ማግኘት በራሱ መብት ከመሆኑም በላይ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብትን ጨምሮ የሰብአዊ ድጋፍን አቅርቦትን ለማሳለጥ፣ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት እና ለሌሎች መብቶች መከበር ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡


### ምዝገባ

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በተመለከተ የተሰባጠረ መረጃ የያዘ መዝገብ ማደራጀትና ወቅታዊ ማድረግ፤ ለተፈናቃዮች የሚደረገውን የሰብአዊ ድጋፍ እና የጥበቃ ዐይነት እንዲሁም መጠኑን በመለየት ተገቢውን ድጋፍና ጥበቃ ለማድረግ፣ ድጋፍ ለማን እንደሚጠየቅ ለማወቅ እና ድጋፍ የሚያደርጉ ድርጅቶችን ሥራ የተቀላጠፈ ለማድረግ እንዲሁም የዘላቂ መፍትሔ ሥራን ለማሳለጥ ጉልህ አስተዋጽዖ አለው፡፡

***በክትትል የተስተዋሉ መልካም ጅማሮዎች፦***

- በትግራይ ክልል ክትትል በተደረገባቸው በአብዛኞቹ መጠለያ/ማቆያ ጣቢያዎች ሁሉንም ተፈናቃዮች ባካተተ መልኩ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት፣ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተፈናቃዮች እንዲሁም የማይድን/ቋሚ የጤና ችግር ያለባቸውን የሚገልጽ የተሰባጠረ መረጃ የያዘ መዝገብ የተደራጀ ሲሆን፤ መረጃዎች በየጊዜው ወቅታዊ እንደሚደረጉ እንዲሁም አብዛኞቹ ተፈናቃዮች ማንነታቸውን የሚገልጽ ጊዚያዊ የመታወቂያ ካርድ የተሰጣቸው መሆኑ፤
- ከ2013 ዓ.ም. ጀምሮ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ከኦሮሚያ እና ከቀድሞው ደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች ተፈናቅለው በአማራ ክልል ባሕር ዳር ከተማ አፄ ቴዎድሮስ እና ዳግማዊ ሚኒልክ ክፍለ ከተሞች ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በከተማ አስተዳደሩ በኩል በ2016 ዓ.ም. ዳግም ምዝገባ በማከናወን መረጃው ለክልሉ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ኮሚሽን እና ሌሎች አካላት የተላከ መሆኑ፤
- ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ተፈናቅለው በተለያዩ የዞኑ ከተሞች ተጠልለው ለሚገኙ ተፈናቃዮች ኢሰመኮ ባደረገው የመጀመሪያ ክትትል እና በሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት የቦራ ወረዳ ቡሳ ጎኖፋ ጽሕፈት ቤት ከባርታ ሳሚ እና ጂርሜ ቦራ ቀበሌዎች የተፈናቀሉ ሰዎችን በቤተሰብ ደረጃ መመዝገባቸው፤ በተመሳሳይ በዚሁ ዞን ከዱግዳ ወረዳ ጀዌ ቦፎ እና ኦዳ ፊላ ቀበሌዎች ከእርሻ መሬት ይዞታዎቻቸው የተፈናቀሉ ሰዎች በዱግዳ ወረዳ ቡሳ ጎኖፋ ጽሕፈት ቤት በቤተሰብ ደረጃ መመዝገባቸው፤
- በሐረሪ ክልል በሐማሬሳ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ እና በሸንኮር ወረዳ የሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ ውስጥ ለሚገኙ ተፈናቃዮች የክልሉ የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራ ምግብ ዋስትና አደጋ መከላከል ጽሕፈት ቤት፣ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ እና ሌሎች ተቋማት በጋራ በመሆን አካታች እና የተሰባጠረ ምዝገባ ማከናወናቸው፤

- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ በኦሞ ወንዝ ሙላት ሳቢያ ከ2012 ዓ.ም. ጀምሮ ለተፈናቀሉ ነዋሪዎች በ2016 ዓ.ም. ዳግም ምዝገባ መደረጉ በመልካም ጎኑ የሚጠቀስ ነው፡፡



*ምስል 1፦ በሐረሪ ክልል በሐማሬሳ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ እና በሸንኮር ወረዳ በሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ ውስጥ ለሚገኙ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ለማመቻቸት በተቋቋመው ኮሚቴ የተደራጀ የተፈናቃዮች መረጃ ማሳያ*

***በክትትል የተለዩ ክፍተቶች፦***

- ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ዱግዳ ወረዳ ወዮ ገብርኤል ቀበሌ ከመጋቢት ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ምዝገባ በወረዳው ቡሳ ጎኖፋ ጽሕፈት ቤት አለመከናወኑ፤
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን በሚገኙ መጠለያ ጣቢያዎች በተደረገው ክትትል የተፈናቃዮች መረጃ በክልሉ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን እና ጣቢያዎቹ በሚገኙባቸው የምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች የሚያዝ መሆኑን ኢሰመኮ በክትትሉ ወቅት የተመለከተ ቢሆንም ለተፈናቃዮቹ የተደረገው ምዝገባ ግን በጾታ፣ ዕድሜ እና የአካል ጉዳት ሁኔታ ተለይቶ አለመከናወኑን፣ መረጃው በየጊዜው ወቅታዊ እንደማይደረግ፣ ያለው መረጃ ወጥ አለመሆኑን እና ሁሉንም ተፈናቃይ ባካተተ ሁኔታ አለመያዙ፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ ለሚገኙ ተፈናቃዮች ምዝገባ የተደረገ ቢሆንም በምዝገባው የተፈናቃዮች መረጃ በጾታ፣ በዕድሜ እና በአካል ጉዳት ተለይቶ በተሰባጠረ መልኩ አለመያዙ ኢሰመኮ በክትትል ከለያቸው ክፍተቶች ዋነኞቹ ናቸው፡፡

## ሰነድ የማግኘት መብት

ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተገቢውን ድጋፍና ጥበቃ ለማድረግ እንዲሁም መብቶቻቸውን መጠቀም እና መተግበር እንዲችሉ ማንነታቸውን የሚገልጹ ሰነዶች እንደ መታወቂያ፣ ወሳኝ ኩነቶችን የተመለከቱ ሰነዶች (የልደት፣ የጋብቻ እና የሞት ምስክር ወረቀቶች) ፣ እንዲሁም ፓስፖርት እንዲያገኙ ማስቻል አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን ሰነዶች ማግኘታቸው ትምህርት፣

ጤና፣ ማኅበራዊ ዋስትና፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብቶቻቸውን ጨምሮ የሲቪል፣ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶቻቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላቸዋል። ተፈናቃዮች እነዚህን ሰነዶች ለማግኘት አለመቻላቸው በራሱ የመብት ጥሰት ሲሆን ሌሎች መብቶቻቸውን ተግባራዊ ከማድረግ በመገደብ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድርባቸዋል።

*በክትትል የተስተዋሉ መልካም ጅማሮዎች:-*

- በትግራይ ክልል በተደረገ ክትትል ለተወሰኑ ተፈናቃዮች ማንነታቸውን የሚገልጽ ጊዜያዊ የመታወቂያ ካርድ የተሰጣቸው መሆኑ በመልካም ጎኑ የሚጠቀስ ነው።

*በክትትል የተለዩ ክፍተቶች፦*

- በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ከቦራ እና ዱግዳ ወረዳዎች ተፈናቅለው በዞኑ የተለያዩ ከተሞች የሚገኙ ተፈናቃዮች ተፈናቃይ መሆናቸውን የሚገልጽ መታወቂያ እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች ተፈናቅለው በሚገኙበት ቦታ አለመሰጠቱ፤
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን በማንቡክ፣ ገነተ ማርያም እና ድባጤ መጠለያ ጣቢያዎች በተደረገው ክትትል ተፈናቃዮች መታወቂያን ጨምሮ ሌሎች የጠፉባቸውን ሰነዶች ለማግኘት እንደሚቸገሩ እና ለዚህም ገንዘብ እንደሚጠየቁ፤ እንዲሁም የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎት ለተፈናቃዮች ባሉበት ቦታ ተደራሽ ማድረግ አለመቻሉ፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ ለሚገኙ አብዛኛዎቹ ተፈናቃዮች ማንነታቸውን የሚገልጽ የቀበሌ መታወቂያ የሌላቸው/ያልተሰጣቸው መሆኑ፤ እንዲሁም በወረዳው ወሳኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎት የሚያገኙ ቢሆንም ተፈናቃዮች የሰነድ ማረጋገጫ (Certificate) የማይሰጣቸው መሆኑ፤
- በሐረሪ ክልል ሸንኮር ወረዳ በሚገኘው የሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ የሚገኙ ተፈናቃዮች በመፈናቀል ወቅት ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ቤታቸው ሲቃጠል አብሮ የጠፋ በመሆኑ እና ማንነታቸውን የሚገልጽ ጊዜያዊ መታወቂያ ስላልተሰጣቸው ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ መቸገራቸው፤
- በትግራይ ክልል አክሱም፣ አድዋ፣ አዲግራት እና ውቅሮ ከተሞች ተጠልለው የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ባሉበት ቦታ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎት የማያገኙ መሆኑ በክትትል ተለይቷል።

## ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ እና የመኖሪያ ቦታን የመምረጥ ነጻነት አላቸው። ከቦታ ቦታ እንዳይንቀሳቀሱ በግልጽ በሕግ የተጣሉ ገደቦች ባይኖሩም በተለያዩ ምክንያቶች ለምሳሌ፦ ማንነትን የሚገልጹ መታወቂያ ባለማግኘታቸው በመንግሥት የጸጥታ አካላት የሚወሰዱ የእስር እርምጃዎች እንዲሁም በተወሰኑ አካባቢዎች ባለው የጸጥታ ችግር እና ተፈናቃዮች ተጠልለው በሚገኙባቸው አካባቢዎች የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ተደራሽ ባለመሆናቸው ምክንያት ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ይቸገራሉ።

*በክትትል የተስተዋሉ መልካም ጅማሮዎች፦*

- በትግራይ ክልል በተለይም ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት በኋላ በክትትሉ በተሸፈኑ አካባቢዎች የሚስተዋሉ የጸጥታ እና ደኅንነት ሥጋቶች አለመኖራቸውን እና ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያ ውስጥም ሆነ ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ያለሥጋት በነጻነት መንቀሳቀሳቸው በመልካም ጎኑ የሚጠቀስ ነው።

***በክትትል የተለዩ ክፍተቶች፦***

- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን በማንቡክ መጠለያ ጣቢያ የሚኖሩ የጉሙዝ ብሔር ተወላጅ ተፈናቃዮች በአካባቢው ካለው የጸጥታ ችግር እንዲሁም በድባጤ ወረዳ መጠለያ ጣቢያ የሚኖሩ ተፈናቃዮች ከመታወቂያ ችግር ጋር በተያያዘ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ የሚቸገሩ መሆኑ፤
- በአሪ ዞን ደቡብ አሪ ወረዳ ቶልታ፣ ሜፀር እና ጋዘር ቀበሌዎች የሚገኙ ተመላሽ ተፈናቃዮች ከአካባቢው ማኅበረሰብ አልፎ አልፎ በሚደርስባቸው ዛቻ እና ማስፈራሪያ ምክንያት በነጻነት ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ እንደሚቸገሩ፤
- ከአማራ ክልል ወደ ኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ እና ምሥራቅ ወለጋ ዞኖች የተመለሱ ተፈናቃዮች ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ የደኅንነት ሥጋት ያለባቸው መሆኑ በክትትል የተለዩ ክፍተቶች ናቸው፡፡

## የጸጥታ፣ ደኅንነት እና ፍትሕ የማግኘት መብት

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እንደማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር እና ከአካላዊ ጉዳት የመጠበቅ፣ ለደረሰባቸው አካላዊም ሆነ ቁሳዊ ጉዳት ተገቢውን ፍትሕ የማግኘት እንዲሁም ከደኅንነት እና ከጸጥታ ሥጋት ነጻ ሆነው የመኖር መብት አላቸው፡፡

***በክትትል የተስተዋሉ መልካም ጅማሮዎች፦***

- በትግራይ ክልል ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት በኋላ ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ይስተዋሉ የነበሩ የጸጥታ እና ደኅንነት ሥጋቶች መቀነሳቸው፤
- በጋምቤላ ክልል ከአኙዋ ዞን ጆር ወረዳ በታጠቁ ኃይሎች ታግተው የተወሰዱ 6 ተፈናቃይ ሕፃናት ተመልሰው ከቤተሰቦቻቸው እንዲገናኙ መደረጉ በመልካም ጎኑ የሚወሰድ ነው፡፡

***በክትትል የተለዩ ክፍተቶች፦***

- ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ቦራ ወረዳ ተፈናቅለው በመቂ ከተማ የሚኖሩ ተፈናቃዮች ከተለያዩ አካላት ዛቻ እና ማስፈራሪያ እንደሚደርሳቸው፣ ለምሳሌ ቃለ መጠይቅ የተደረጋላቸው ተፈናቃይ ያለውን ሁኔታ ሲያስረዱ *"በኅዳር ወር 2016 ዓ.ም. የታጠቁ ቡድኖች አባላት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ከተማ ገብተው 4 ተፈናቃዮችን በአንድ አካባቢ መግደላቸው በነጻነት በፈለግነው ሰዓት ለመንቀሳቀስ ሥጋት ፈጥሮብናል፡፡ ጥቃቱን የፈጸሙ ሰዎችም ተይዘው ለሕግ አልቀረቡም፡፡"* በማለት ፍትሕ ያላገኙ መሆኑን፤ በተጨማሪም ከቦራ ወረዳ ባርታ ሳሚ እና ጂርሜ ቦራ ቀበሌ እንዲሁም ከዱግዳ ወረዳ ወዮ ገብርኤል ቀበሌ ተፈናቅለው ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ተፈናቃዮች በአከባቢው የሚንቀሳቀሰው ራሱን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በማለት የሚጠራው ታጣቂ ቡድን (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") የደኅንነት ሥጋት ያሳደረባቸው መሆኑ፤
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን በማንቡክ ተጠልለው ለሚገኙ ተፈናቃዮች በአካባቢው ላይ የጸጥታ ሥጋት ያለ ቢሆንም ተገቢው ጥበቃ የማይደረግላቸው በመሆኑ ግድያ፣ የሴቶች ጠለፋ እና የእርስ በእርስ ጥቃቶች መፈጸማቸው፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ የሚገኙ ተፈናቃዮች መነሻቸውን ከኬንያ ቱርካና ሐይቅ ዳርቻ ካደረጉ አርብቶ አደሮች ጋር አልፎ አልፎ ግጭት ውስጥ እንደሚገቡ እና ይህም በደኅንነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረባቸው መሆኑ፤

በተጨማሪም የኦሞ ወንዝ ሙላት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት በመጠለያ የሚገኙ ተፈናቃዮች የደኅንነት ሥጋት ያለባቸው መሆኑ፤

- በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ጃራ መጠለያ ካምፕ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ክልሉን አልፈው በሚመጡ ታጣቂዎች በተደጋጋሚ ጥቃት የሚደርስባቸው በመሆኑ የደኅንነት ሥጋት ያለባቸው መሆኑ፤
- ከኦሮሚያ ክልል ተፈናቅለው በአማራ ክልል የተለያዩ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎችና አካባቢዎች ለሚገኙ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት ሁለቱ ክልሎች በተስማሙት መሠረት ወደ ኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ዞኖች ተፈናቃዮች የሰፈሩባቸው እና ይመለሱባቸዋል ተብለው የተለዩ አካባቢዎች አሁንም አሳሳቢ የጸጥታ ችግር እንዳለባቸው፣ ተፈናቃዮች ወደ እነዚህ ስፍራዎች ቢመለሱ ለደኅንነት ሥጋት እና ለዳግም መፈናቃል ሊጋለጡ እንደሚችሉ ኢሰመኮ በክትትሉ የለያቸው ክፍተቶች ናቸው::

## የሰብአዊ ድጋፍ የማግኘት መብት

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ህልውናቸውን ለማስቀጠል እና መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት አስፈላጊ የሆኑ የምግብ፣ መጠለያ፣ አልባሳት እና ሌሎች ቁሳቁሶች ድጋፍ የማግኘት መብት አላቸው:: ተፈናቃዮች ቤታቸውን እና ንብረታቸውን ጥለው ከሚኖሩበት ቀዬ ሕይወታቸውን ለማትረፍ የሚሸሹ በመሆኑ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን በራሳቸው ለማሟላት ይቸገራሉ::

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በመንግሥት በጀት በሚደገፉ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት ያላቸው ቢሆንም ካሉበት የመፈናቀል ሁኔታ አንጻር ከሌሎች እኩል አገልግሎቶቹን ማግኘት ባለመቻላቸው ለተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ ናቸው::

### ምግብ፣ ውሃ፣ መጠለያ እና አልባሳት

***በክትትል የተስተዋሉ መልካም ጅማሮዎች፦***

- በትግራይ ክልል ለሚገኙ ተፈናቃዮች ተቋርጦ የነበረው የምግብ ድጋፍ ከመስከረም ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በፌዴራል አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በኩል እንደገና መጀመሩ፤
- በሐረሪ ክልል ሐማሬሳ የተፋናቃዮች መጠለያ ጣቢያ ይኖሩ ለነበሩ 27 ተፈናቃይ ቤተሰቦች በየወረዳቸው የቀበሌ ቤት መሰጠቱ፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በአሪ ዞን ደቡብ አሪ ወረዳ በቶልታ፣ ሜፀር እና ጋዘር ቀበሌዎች ተፈናቃዮችን በዘላቂነት መልሶ ለማቋቋም የክልሉ መንግሥት የአካባቢውን ማኅበረሰብ ጨምሮ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር 103 በግጭት የወደሙ ቤቶችን ግንባታ መጀመሩ፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች ወረዳ ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለሁሉም ተፈናቃዮች በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የገንዘብ እና የምግብ ድጋፍ መደረጉ በመልካም ጎኑ የሚጠቀስ ነው::

***በክትትል የተለዩ ክፍተቶች፦***

- በትግራይ ክልል የተፈናቃዮች የምግብ ድጋፍ አቅርቦት ለተከታታይ 7 ወራት ተቋርጦ በነበረ ጊዜ ተፈናቃዮች ለርሃብ መዳረጋቸውን በተለይም ከ1 እስከ 5 ዓመት የሆኑ ሕፃናት ለከፍተኛ የምግብ እጥረት (malnutrition) መጋለጣቸው፤ በተጨማሪም በመጠለያ ችግር ምክንያት አብዛኛዎቹ ተፈናቃዮች በትምህርት ቤቶች፣ በጤና ጣቢያ እና በግለሰብ መጋዘኖች በተጨናነቀ ሁኔታ ተጠልለው የሚገኙ በመሆኑ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች እንዲሁም ሴቶችን ለጾታዊ ጥቃት እንዲጋለጡ መደረጉ፤
- ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ቦራ ወረዳ ባርታ ሳሚ (አውራጎዳና) እና ጂርሜ ቦራ ቀበሌዎች ተፈናቅለው በዞኑ የተለያዩ ከተሞች ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ተፈናቃዮች ከተፈናቀሉበት ጊዜ ጀምሮ በመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ምንም ዐይነት የምግብ፣ የመጠለያ፣ የአልባሳት እና ሌሎች ቁሳቁሶች ድጋፍ ያልተደረገላቸው በመሆኑ በከፋ ችግር ውስጥ መሆናቸው፤
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን በክልሉ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በኩል ለተፈናቃዮቹ ሲቀርብ የነበረው የምግብ ድጋፍ በማንቡክ መጠለያ ጣቢያ ከ2 ዓመት በላይ፤ በድባጤ መጠለያ ጣቢያ ከ1 ዓመት ከ3 ወር በላይ እና በገነተ ማርያም ደግሞ ከ3 ዓመታት በላይ በመቋረጡ ምክንያት ሴቶች፣ ሕፃናት እና አረጋውያንን ጨምሮ በመጠለያ ጣቢያዎች ያሉ ተፈናቃዮች ለከፋ ችግር መዳረጋቸው፤ በዚህም ተፈናቃዮች የቀን ሥራ በመሥራት እና ከተራድኦ ድርጅቶች በሚያገኙት የቁሳቁስ ድጋፍ ብቻ ኑሯቸውን እየገፉ መሆኑን፤ በተጨማሪም የማንቡክ እና ገነተ ማሪያም መጠለያ ጣቢያዎች በቂ የሆነ የመጠጥ እንዲሁም የንጽሕና መጠበቂያ ውሃ አቅርቦት አለመኖር እንዲሁም የመጠለያ ሸራዎች በቆይታ ብዛት ከጥቅም ውጭ መሆናቸው፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች ወረዳ በተደረገ ክትትል ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በቂና ወቅቱን የጠበቀ የምግብ ድጋፍ ስለማይቀርብላቸው ለርሃብ የተጋለጡ መሆኑን፤ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት አለመኖሩን፤ በግጦሽ እጥረት ምክንያት ከብቶቻቸው በርሃብ እየሞቱባቸው መሆኑን፤ የመጠለያ ሸራ ድጋፍ ለሁሉም ተፈናቃዮች አለመዳረሱ፤
- በሶማሊ ክልል ፋፈን ዞን ጎልጃኖ ከተማ በዘላቂነት እንዲሰፍሩ የተደረጉ ተፈናቃዮች የምግብ ድጋፍ የተቋረጠባቸው መሆኑን፤ የአብዛኛዎቹ ተፈናቃዮች በዓለም የምግብ ፕሮግራም (WFP) የተሰጣቸው የምግብ መቀበያ ካርድ/ኩፖን የተሰረዘ ሲሆን፣ ከ823 ቤተሰቦች መካከል ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ የምግብ ድጋፍ የሚያገኙት 46 ቤተሰቦች ብቻ መሆናቸው፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አሪ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ተፈናቅለው ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው ለሚኖሩ ተፈናቃዮች ተገቢው የሰብአዊ ድጋፍ ባለመደረጉ ለከፋ ችግር በተለይም ለምግብ እጥረት መጋለጣቸው፤
- ከማይካድራ፣ ሁመራ እና ዳንሻ አካባቢዎች በሰሜኑ ጦርነት ሳቢያ ተፈናቅለው በማእከላዊ ጎንደር፤ ሰሜን ጎንደር እና ደቡብ ጎንደር የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ምንም ዐይነት የዘላቂ መፍትሔ አማራጭ ባልተመቻቸበት ሁኔታ "አሁን ላይ አካባቢዎቹ ሰላም በመሆናቸው ወደመጡበት መመለስ ይችላሉ" በማለት የአማራ ክልል መንግሥት የሰብአዊ ድጋፍ በማቋረጡ ለችግር መጋለጣቸው፤
- በአማራ ክልል ምሥራቅ እና ምዕራብ ጎጃም ዞኖች በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ከመስከረም ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ምንም ዐይነት የምግብ እና መጠለያ ድጋፍ እያገኙ አለመሆኑ፤ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ዞኖች ተፈናቅለው በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን ጎንደር

እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ እና ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ተፈናቃዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለይም መንግሥት ተፈናቃዮችን ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው ለመመለስ እንቅስቃሴ ማድረግ ከጀመረ ወዲህ፣ በመንግሥት እና በተራድኦ ድርጅቶች በኩል ይቀርብ የነበረው የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ድጋፍ በመጠንም ሆነ በዐይነት በጣም እየቀነሰ መምጣቱ፤

- በጋምቤላ ክልል የአኙዋ ብሔረሰብ ዞን ጆር ወረዳ የሚገኙ ተፈናቃዮች የተጠለሉት በትምህርት ቤት ውስጥ በመሆኑ በማይመች ሁኔታ የትምህርት ቤት ክፍሎች ውስጥ እና በረንዳ ላይ የሚተኙ እንዲሁም የአልባሳት እና የሌሎች ቁሰቁሶች ድጋፍ ያልተደረገላቸው በመሆኑ በአሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ መገኘታቸው፤
- በሐረሪ ክልል ሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ እና ሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ግቢ ውስጥ ለሚገኙ ተፈናቃዮች የሚቀርበው የምግብ ድጋፍ ተከታታይነት የሌለው እና በመጠንም ሆነ በዐይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱ ወይም ከተቀመጠው መስፈርት በታች መቅረቡ፤ በተጨማሪም በሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ ለሚገኙ ተፈናቃዮች ይቀርብ የነበረው የውሃ እና የመብራት አቅርቦት ከተቋረጠ 3 ዓመታት ማለፉን፤
- በሐረሪ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ ተፈናቃዮች የሚኖሩት፤ ለሴቶችና ወጣት ተጠርጣሪዎች ማቆያ ተብሎ በተዘጋጁ ክፍሎች በመሆኑ ተጠልለው የሚገኙበት ቦታ ለሕፃናት ተፈናቃዮች እድገት ምቹ አለመሆኑ፤ እንዲሁም ክፍሎቹ ለሁሉም ተፈናቃዮች በቂ ባለመሆናቸው አንዳንዶቹ ተፈናቃዮች በቢሮ በረንዳ ላይ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ መሆኑ፤
- ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ካፋ ዞን ዴቻ ወረዳ ሥራ ሕይወት እና ገነት የሰፈራ ጣቢያዎች ተፈናቅለው በካምባታ ጣምባሮ ዞን አንገጫ እና ዶዮ ገና ወረዳ በዘመድ ቤት በጥገኝነት፤ እንዲሁም በቤት ኪራይ እየኖሩ የሚገኙ ተፈናቃዮች የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት ከ2012 ዓ.ም. ጀምሮ የተቋረጠባቸው በመሆኑ በጉልበት ሥራ እራሳቸውን ለማስተዳደር መገደዳቸውን እና ለከፋ ችግር መዳረጋቸውን ኢሰመኮ በክትትል የለያቸው ክፍተቶች ናቸው።



*ምስል 2፦ በሐረሪ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ የተፈናቃዮች እየኖሩ ያለበት ሁኔታ ማሳያ*



*ምስል 3፡ ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን ለተመላሽ ተፈናቃዮች የተዘጋጃ ጊዜያዊ መጠለያ*

## የማኅበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት

### *በክትትል የተስተዋሉ መልካም ጅማሮዎች፦*

- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች ወረዳ ተፈናቃዮች ተጠልለው በሚገኙበት አካባቢ በመንግሥት እና በግብረሰናይ ድርጅቶች ድጋፍ የተሠሩ ጊዜያዊ የትምህርት መስጫ ማእከላት በመኖራቸው ተፈናቃይ ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማግኘት መቻላቸው፤
- በሐረሪ ክልል ሐማሬሳ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች የሐኪም ወረዳ አስተዳደር ባመቻቸው የጤና መድን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸው ፤
- ክትትል በተደረገባቸው የተወሰኑ አካባቢዎች ለምሳሌ በአማራ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና ሶማሊ ክልሎች ተፈናቃይ ተማሪዎች ባሉበት ቦታ ከተቀባይ ማኅበረሰብ ተማሪዎች ጋር ተቀላቀው ትምህርታቸውን መከታተላቸው፤ በአካባቢው በሚገኙ የጤና ተቋማት በራሳቸው ወጭ የሕክምና አገልግሎት እንዲሁም ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ከአካባቢው ማኅበረሰብ እኩል ማግኘት መቻላቸው በበጎ ጎኑ የሚወሰድ ነው።

### *በክትትል የተለዩ ክፍተቶች፦*

- በትግራይ ክልል 110 ትምህርት ቤቶች የተፈናቃይ መጠለያዎች በመሆናቸው የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዳስተጓጎለና በትምህርት ተደራሽነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ፤ ተፈናቃይ ተማሪዎች በከፊል ትምህርት በጀመሩ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ቢሆንም በምግብ እና በትምህርት ቁሳቁስ እጥረት ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመከታተል መቸገራቸው፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች ወረዳ የሚገኙ ተፈናቃዮች በአካባቢው በሚገኙ የመንግሥት የጤና ተቋማት በክፍያ ሕክምና የሚያገኙ ሲሆን የገንዘብ ዐቅም የሌላቸው (የጤና መድን መዋጮ መክፈል ያልቻሉ) የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት እንደሚቸገሩ፤ በተጨማሪም የሚኖሩበት አካባቢ በውሃ የተከበበ በመሆኑ የወባ በሽታ

ስርጭት መኖሩን እና ለዚህም አስፈላጊው የሕክምና እና የመከላከያ ቁሳቁስ ድጋፍ አለመደረጉ፤

- በጋምቤላ ክልል ክትትል በተደረገባቸው በኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ጂካዎ፣ ጋምቤላ ዙሪያ እና ጆር ወረዳዎች በጎርፍ መጥለቅለቅ ሳቢያ በሰብል ምርት እና በእንስሳት ሀብት ላይ ጉዳት መድረሱ፤ በአገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይም ለምሳሌ በኢታንግ ልዩ ወረዳ እና ጂካዎ ወረዳ በሚገኙ ጤና ጣቢያዎች፤ እንዲሁም በጅካዎ ወረዳ የሚገኝ መኮይ ትምህርት ቤት በውሃ በመከበባቸው የትምህርት እና የጤና አገልግሎት ለአንድ ወር ያህል ተቋርጦ የቆየ መሆኑ፤
- በጋምቤላ ክልል አኙዋ ዞን ጆር ወረዳ ከተለያዩ ቀበሌዎች ተፈናቅለው በአሌላ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በመጠለላቸው ምክንያት በትምህርት ቤቱ ይማሩ የነበሩ 979 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች ትምህርታቸው ለማቋረጥ የተገደዱ መሆኑ፤ በተጨማሪም በዚሁ ወረዳ ይገኙ የነበሩ ኡቶል 01፣ ኡሚንጋ፣ ኡቶል 02 እና አሌሮ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ኡሚንጋ 01 ጤና ኬላ ሙሉ በሙሉ በመውደማቸው 810 የሚሆኑ ተማሪዎች ትምህርት ለማቋረጥ መገደዳቸው እና የጤና አገልግሎት መስተጓጎሉ፤
- በሶማሊ ክልል ፋፋን ዞን ቀብሪ በያህ ወረዳ ዱርዋሌ ቀበሌ በዘላቂነት እንዲሰፍሩ የተደረጉ ተፈናቃዮች ከቀብሪ በየህ ከተማ ዕርቀው በመስፈራቸው እና ከተማ ለመሄድ የመንገድ መሠረተ ልማት የሌለ በመሆኑ የትምህርት እና ጤናን ጨምሮ የተለያዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት መቸገራቸውን፤
- ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ከቦራ ወረዳ ባርታ ሳሚ እና ጂርሜ ቦራ ቀበሌዎች እና ከዱግዳ ወረዳ ወዮ ገብርኤል ቀበሌ ተፈናቀለው በዞኑ የተለያዩ ከተሞች ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው እየኖሩ ለሚገኙ ተፈናቃዮች ምንም ዐይነት የሰብአዊ ድጋፍ ባለመኖሩ፣ ሕፃናት ተማሪዎች ከመማር ይልቅ ቤተሰባቸውን እና እራሳቸውን ለመደገፍ ለጉልበት ብዝበዛ በሚያጋልጧቸው ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ከትምህርት ገበታ ውጪ መሆናቸው፤ በተጨማሪም ከቦራ ወረዳ የተፈናቀሉ ሰዎች በመፈናቀል ሂደት የጤና መድሕን ካርዳቸውን በማጣታቸው የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት መቸገራቸውን፤
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን ለሚገኙ ተፈናቃዮች በመንግሥት በኩል ነጻ የሕክምና አገልግሎት እንደማይቀርብ፤ በምግብ እና በትምህርት ቁሳቁስ እጥረት ሳቢያ ተፈናቃይ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመከታተል እንደሚቸገሩ፤
- በሐረሪ ክልል ሸንኮር ወረዳ ሐረሪ ፖሊስ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ የሌላቸው በመሆኑ የጤና መድኅን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳልሆኑ፤ በዚህም ነጻ የጤና አገልግሎት ማግኘት ባለመቻላቸው በራሳቸው የሕክምና ወጪያቸውን ለመሸፈን እንደተቸገሩ፤ በተጨማሪም በአካባቢው ያሉ ትምህርት ቤቶች ለተፈናቃይ ተማሪዎች ተደራሽ ቢሆኑም ለተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ የማይደረግ በመሆኑ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመከታተል መቸገራቸው፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አሪ ዞን ከተለያዩ ወረዳዎች ተፈናቅለው ጂንካ ከተማ የሚገኙ እንዲሁም ንብረታቸው በመውደሙ በመኖሪያ አካባቢያቸው በግለሰብ ቤት ተጠልለው አሊያም ተከራይተው የሚገኙ ተመላሽ ተፈናቃይ ተማሪዎች በትምህርት ቁሳቁስ እጥረት እና ለመማር ምቹ ሁኔታ ባለመፈጠሩ ምክንያት አብዛኞቹ ከትምህርት ገበታ ውጭ መሆናቸውን፤

- በተወሰኑ አካባቢዎች በተለይም በአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች ያለው ግጭት በሚፈጥረው የትራንስፖርት መስተጓጎል እና የሕክምና ግብአቶች እጥረት ምክንያት የጤና ተቋማት ለተፈናቃዮች ተደራሽ አለመሆናቸው በክፍተትነት ተለይተዋ።




*ምስል 4፡- ተፈናቃዮች ተጠለለው የሚገኙበት የአሌሳ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት (ጆር ወረዳ)*

## ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች

- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈጋልቸው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በተለይም ከቤተሰባቸው ለተለዩ እና ጠባቂ የሌላቸው ሕፃናት፣ ሴት የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች፣ ነፍሰጡሮች፣ ጨቅላ ሕፃናት ያሏቸው እናቶች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች እና የማይድን/ቋሚ የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች ካሉበት የመፈናቃል ሁኔታ በተጨማሪ ከሌሎች ተፈናቃዮች የበለጠ ለመብት ጥሰት እና ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ በመሆናቸው ልዩ ድጋፍ እና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል።

***በክትትል የተስተዋሉ መልካም ጅማሮዎች፦***

- በትግራይ ክልል ለሚገኙ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተፈናቃዮች በተራድዖ ድርጅቶች አማካኝነት ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ድጋፍ እንዲሁም በተወሰኑ መጠለያ ጣቢያዎች ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የሕክምና እና የሥነ-ልቦና ድጋፍ መደረጉ፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች ወረዳ ለሚገኙ ተፈናቃዮች የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን በክልሉ ሴቶችና ሕፃናት ቢሮ በኩል ለተፈናቃዮች የአልባሳት፣ ጫማ፣ ዱቄት፣ ቦቆሎ እና የምግብ ዘይት ድጋፍ ያደረገ መሆኑን፤ እንዲሁም የክልሉ ሴቶችና ሕፃናት ቢሮ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተፈናቃዮች የ5 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ ከዓለም አቀፍ የተራድዖ ድርጅቶች በማሰባሰብ ድጋፍ መደረጉ፤
- በጋምቤላ ክልል በጎርፍ መጥለቅለቅ ሳቢያ ለተፈናቀሉ ሰዎች በተለያዩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተጎጂዎች የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ጨምሮ የተለያዩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ድጋፍ መደረጉ በመልካም ጎኑ የሚጠቀስ ነው።




*ምስል 5፡ በጎርፍ ለተፈናቀሉና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ልየታ ሥራ ላይ (ጋምቤላ ዙሪያ ወረዳ)*

***በክትትል የተለዩ ክፍተቶች፦***

- በትግራይ ክልል አክሱም 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተጠልለው የሚገኙ ሴት ተፈናቃዮች የንጽሕና መጠበቅያ ቁሳቁስ ድጋፍ የተቋረጠባቸው መሆኑ፤ በተለያዩ የተራድዖ ድርጅቶች አማካኝነት የወሊድ ክትትል፣ የሕፃናት ክትባት፣ የሥነ-ተዋልዶ ጤና እና ጥቃት ለደረሰባቸው የሥነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ቢሆንም፣ በክትትሉ ወቅት "ትምህርት ሊጀመር ስለሆነ" በሚል ምክንያት ድርጅቶቹ አገልግሎቱን የሚሰጡበትን የመማሪያ ክፍሎች እንዲለቁ መደረጉ፣ በዚህም ምክንያት በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ አገልግሎቱ የሚሰጥ ቢሆንም ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ ምቹ አለመሆኑ፤ ሕፃናት ለልመና ወደ ወታደር ካምፕ እና የተለያዩ ሥፍራዎች በሚሄዱበት ጊዜ ጥቃት የሚደርስባቸው መሆኑ፤
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን በድባጤ፤ ገነተ ማርያም እና ማንቡክ ወረዳዎች በሚገኙ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ የተፈናቃዮችን ተጋላጭነት እና ፍላጎት መሠረት ያደረገ ድጋፍ ባለመደረጉ ዕድሜያቸው የገፋ አረጋውያን፣ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ለርሃብ እና በሽታ መዳረጋቸውን፤ እንዲሁም የወላድ እናቶች የሕክምና ክትትል አገልግሎት በነጻ የማይሰጥ በመሆኑ አገልግሎቱን ለማግኘት መቸገራቸውን፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች ወረዳ ለተደራራቢ የመብት ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ ሕፃናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተፈናቃዮች በቂ እና ልዩ ፍላጎታቸውን ያማከለ ድጋፍ እንደማይቀርብ፤ በዚህም ሕፃናት ተፈናቃዮች ምግብ ለማግኘት ለሕይወታቸው አስጊ በሆነ ሁኔታ ጥልቅ ውሃ ውስጥ እየገቡ ዓሳ በማጥመድ ረሀባቸውን ለማስታገስ እንደሚጥሩ፤
- በጋምቤላ ክልል አኙዋ ዞን ጆር ወረዳ የሚገኙ ልዩ ድጋፍ እና ጥበቃ ለሚሹ ተፈናቃዮች በተለይም ከቤተሰቦቻቸው ለተለዩ እና ጠባቂ ለሌላቸው ሕፃናት፣ ለሴት የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች፣ ለነፍሰጡሮች፣ ለሚያጠቡ እናቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ልዩ ፍላጎታቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባ ድጋፍ አለመኖሩን፤
- በሐረሪ ክልል ሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ እና ሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ግቢ ውስጥ ለሚገኙ ተፈናቃዮች የሚቀርበው የምግብ ድጋፍ ተከታታይነት የሌለው እና በመጠንም ሆነ

በዐይነት እየቀነሰ መምጣቱን፣ በተለይም የነፍሰ ጡር ሴቶች፣ የሕፃናት፣ ተጓዳኝ ሕመም ያለባቸው፣ የአካል ጉዳተኞች እንዲሁም የአረጋውያን ተፈናቃዮች ሁኔታን ከግምት ያላስገባ በመሆኑ ለምግብ እጥረት መጋለጣቸው በክትትል የተለዩ ክፍተቶች ናቸው፡፡

## የቤት፣ መሬት እና ንብረት መብት

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ወደ ቀድሞ የመኖሪያ ቦታ በመመለስ ወይም ወደ ሌላ ቦታ በማስፈር በዘላቂነት እንዲቋቋሙ በሚደረግ ጊዜ በመፈናቀል ወቅት ያጡትን ቤት፣ መሬት እና ሌሎች ንብረቶች መልሰው ወይም ምትክ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

***በክትትል የተስተዋሉ መልካም ጅማሮዎች፦***

- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ካፋ ዞን ዴቻ ወረዳ በ2011 ዓ.ም. ተፈናቅለው የቆዩ 63 ቤተሰቦች በሕገ ወጥ መንገድ የተያዙ ቦታዎችን የማስለቀቅ፣ ያልተያዙ መሬቶችን የመለየት እና መሬታቸው ለልማት ሥራ ለተወሰደባቸው ተፈናቃዮች ተለዋጭ መሬት የማዘጋጀት ሥራ መከናወኑ፤
- በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ እና ምሥራቅ ወለጋ ዞኖች የተለያዩ ወረዳዎች በተደረገው ክትትል በግጭት ወቅት የወደሙ የተፈናቃዮችን መኖሪያ ቤቶች መልሶ የመገንባት እና የመጠገን እንዲሁም በሌሎች ሰዎች የተያዙ ቤቶችን እና የእርሻ መሬት የማስለቀቅ ሥራዎች የተጀመሩ መሆኑ፤
- በሐረሪ ክልል በሐማሬሳ የተፋናቃዮች መጠለያ ጣቢያ ተጠልለው ይኖሩ ለነበሩ 27 ቤተሰቦች በየወረዳቸው የቀበሌ ቤት መሰጠቱ፤ እንዲሁም በዚሁ ክልል አሚር ኑር ወረዳ ገንደፌሮ እየተባለ ከሚጠራ አካባቢ ተፈናቅለው በሸንኮር ወረዳ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ ለሚገኙ ተፈናቃዮች የወደሙባቸውን ቤቶች መሥራት መጀመሩ፤
- በሶማሊ ክልል ፋፈን ዞን ዱሩዋሌ ቀበሌ እና ጎልጃኖ ከተማ በዘላቂነት እንዲሰፍሩ ለተደረጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቤት ተሠርቶ የተሰጣቸው ሲሆን፣ ይህም ተፈናቃዮች ደኅንነታቸው እና ክብራቸው በተጠበቀ መልኩ እንዲኖሩ እንዳስቻላቸው፤ በተጨማሪም 800 ሄክታር የእርሻ መሬት በዱሩዋሌ ለሚገኙ ተፈናቃዮች ለመስጠት በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑ በበጎ ጎን የሚወሰድ ተግባር ነው፡፡




*ምስል 6፡- በሐኪም ወረዳ የቀበሌ ቤት ከተሰጣቸው ተፈናቃይ ቤተሰቦች መካከል*



*ምስል 7፦ በሐረሪ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ ለሚገኙ ተፈናቃዮች፣ በአሚር ኑር ወረዳ ገንደፌሮ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የተጀመሩ ቤቶች*



*ምስል 8፡ በሶማሊ ክልል ጎልጃኖ ወረዳ ለሰፈሩ ተፈናቃዮች የተሠሩ መኖሪያ ቤቶች*

***በክትትል የተለዩ ክፍተቶች፦***

- በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ከዱግዳ ወረዳ ጀዌ ቦፎ እና ኦዳ ፊላ ቀበሌዎች ከእርሻ መሬት ይዞታቸው የተፈናቀሉ የመቂ ከተማ ነዋሪዎች እንዲሁም ከቦራ ወረዳ ባርታ ሳሚ እና ጂርሜ ቦራ ቀበሌዎች ሙሉ ለሙሉ ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች የእርሻ መሬት በ2015/2016 ዓ.ም. የእርሻ ዘመን በአካባቢው በሚንቀሳቀሰው ራሱን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በማለት በሚጠራው ታጣቂ ቡድን (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) እንቅስቃሴ በተፈጠረ የሰላምና የጸጥታ ሥጋት መነሻነት አለመታረሱን ምክንያት በማድረግ፣ የዱግዳ እና የቦራ ወረዳ አስተዳደሮች በአካባቢው የሰላም ማስከበር ሥራዎችን በመሥራት ላይ ያለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መከላከያ ሰራዊት የተፈናቃዮችን የእርሻ መሬት ይዞታ ተፈናቃዮች ፈቃዳቸውን በግልጽ ባልሰጡበት ሁኔታ በጊዜያዊነት እንዲያርስ እና እንዲጠቀም በመወሰናቸው፤ የዱግዳ ወረዳ ጀዌ ቦፎ እና ኦዳ ፊላ ቀበሌ ተፈናቃዮች የእርሻ መሬት ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ በመከላከያ ሰራዊት መታረሱን፣ የቦራ ወረዳ ባርታ ሳሚ እና ጂርሜ ቦራ ቀበሌ የተፈናቃዮች የእርሻ መሬት በተወሰነ መልኩ መታረስ መጀመሩ፤ በተጨማሪም

ከተፈናቃዮች የእርሻ መሬት ይዞታ የሚገኘውን ምርት በተመለከተ በተፈናቃዮች፣ በወረዳው የመንግሥት አካላት እና በመከላከያ ሰራዊት መካከል በግልጽ የተደረገ የክፍፍል ስምምነት አለመኖሩ፤ እንዲሁም የመሬት ይዞታቸው ድንበር ተቀላቅሎ በመታረሱ የይዞታ መብታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ፤

- በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ በመፈናቀል ወቅት በንብረት ላይ ውድመት መድረሱን፤ እንዲሁም የተፈናቃዮች መኖሪያ ቤቶች እና የእርሻ መሬት ይዞታዎች በሌሎች ሰዎች ተይዘው የሚገኙ መሆኑ፤
- ከሐረሪ ክልል አሚር ኑር ወረዳ ገንደፌሮ እየተባለ ከሚጠራ አካባቢ ተፈናቅለው በሸንኮር ወረዳ ፖሊስ ኮሚሽን ቅጥር ግቢ ለሚገኙ ተፈናቃዮች የወደሙባቸውን ቤቶች መሥራት የተጀመረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ግንባታው የቆመ መሆኑ፤
- የትግራይ ታጣቂ ቡድኖች ወደ ራያ እና ኮረም ከተማ አስተዳድሮች፤ ራያ አላማጣ፣ ዛታ እና ኦፍላ ወረዳዎች መንቀሳቀሳቸውን ተከትሎ በደኅንነት ሥጋት ነዋሪዎች ከመኖሪያ ቦታቸው መፈናቀላቸውን እና በመፈናቀል ወቅት በታጠቁ ኃይሎች የንብረት ዘረፋ እና ውድመት መፈጸሙ በክትትል የተለዩ ክፍተቶች ናቸው፡፡

## ዘላቂ መፍትሔ

በመፈናቀል ጊዜ ከሚደረገው ጥበቃና ድጋፍ በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የዘላቂ መፍትሔ ተጠቃሚ መሆን አለባቸው፡፡ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔን የማመቻቸት ሂደት የተፈናቃዮች ደኅንነትና ክብርን በጠበቀ መልኩ እንዲሁም በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን፤ በተቻለ መጠን የተፈናቃዮችን የቀደሞ መተዳደሪያና ችሎታን መሠረት ያደረጉ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ለመፈናቀል ችግር ዘላቂ መፍትሔዎችን ማፈላለግና መተግበር ያስፈልጋል፡፡

***በክትትል የተስተዋሉ መልካም ጅማሮዎች፦***

- በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን የቦራ ወረዳ አስተዳደር ከባርታ ሳሚ እና ጂርሜ ቦራ ቀበሌዎች የተፈናቀሉ ሰዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም በማሰብ በሚያዚያ 13 ቀን 2016 ዓ.ም. ተፈናቃዮቹን ወደ ተፈናቀሉበት ቀበሌ በመውሰድ እና የዕርቅ ሥነ ሥርዓት በማካሄድ ከተፋናቃዮች 30 ሰዎችን እንዲሁም ከአካባቢው ነዋሪዎች 30 ሰዎችን በመመልመል አካባቢያቸውን እንዲጠብቁ ወታደራዊ ስልጠና እየተሰጣቸው መሆኑ፤
- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ ለሚገኙ ተፈናቃዮች የክልሉ መንግሥት ከክልል እስከ ቀበሌ የአስቸኳይ ምላሽ እና የመልሶ ማቋቋም ሥራዎችን የሚያሳልጥ ኮሚቴ/አደረጃጀት በማዋቀርና ባለድርሻ አካለትን በማሳተፍ ለተፈናቃዮች አስቸኳይ ምላሽ ለመስጠት እና በዘላቂነት ለማቋቋም ጥረት እየተደረገ መሆኑ፤
- ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ካፋ ዞን ዴቻ ወረዳ የተፈናቀሉ 63 ቤተሰቦች ወደ ቀድሞ ቀያቸው መመለሳቸው እና በመፈናቀላቸው ምክንያት ለተወሰደባቸው የእርሻ መሬት ምትክ መሰጠቱ፤
- ከኦሮሚያ ክልል ተፈናቅለው በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ተጠልለው የሚገኙ ተፈናቃዮችን ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው በመመለስ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት በሚደረገው ሂደት ላይ ተፈናቃዮችን እና ተወካዮቻቸውን ያሳተፉ ውይይቶች መደረጉ፤ እንዲሁም የተፈናቃዮች ተወካዮች የሚመለሱባቸውን አካባቢዎች አሁናዊ ሁኔታ በቦታው ተገኝተው እንዲመለከቱ መደረጉ፤

- በሐረሪ ክልል ሐማሬሳ መጠለያ ጣቢያ እና ሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ግቢ ውስጥ ለሚገኙ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔን ለማመቻቸት የመልሶ ማቋቋም ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራ መጀመሩ እና ሂደቱን ለማሳለጥ የሚረዳ ዕቅድ በኮሚቴው መዘጋጀቱ፤
- በሶማሊ ክልል ፋፈን ዞን ዱርዋሌ እና ጎልጃኖ በዘላቂነት እንዲሰፍሩ የተደረጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በዚህ ቦታ ከመስፈራቸው በፊት በክልሉ የሚዛመዱትን ጎሳ ለይተው እንዲሰፍሩ (clan-affiliated relocation) መደረጉን እና በቀላሉ ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር እንዲዋሐዱ ለማስቻል እየተሠራ መሆኑ በመልካም ጎኑ የሚጠቀስ ነው፡፡

*በክትትል የተለዩ ክፍተቶች፦*

- ከቃፍታ ሑመራ፣ ወልቃይት፣ ፀገዴ እና አቅራቢያ ካሉ አካባቢዎች እንዲሁም ከራያ ኣላማጣና አካባቢው ተፈናቅለው ትግራይ ክልል የሚገኙ ተፈናቃዮች “መሬታቸው፣ ቤታቸው እና ሌሎች ንብረቶቻቸው በሌሎች ሰዎች ተይዘዋል” በሚል እና የጸጥታ ሁኔታውም ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ አስተማማኝ የሚባል ባለመሆኑ፤ በተመሳሳይ ከሰሜን ምዕራብ ትግራይ ድንበር አካባቢዎች ከሽራሮ፣ ዛላምበሳና አካባቢው የተፈናቀሉ ሰዎች “በእነዚህ አካባቢዎች የኤርትራ መንግሥት ወታደሮች ይገኛሉ” በሚል የደኅንነት ሥጋት በመኖሩ፤ እንዲሁም ከአፋር ክልል አብዓላ፣ በረሃሌ እና ኮነባ ወረዳዎችና የተለያዩ አካባቢዎች ተፈናቅለው በመቀሌ ከተማ የሚገኙ ተፈናቃዮች “በአካባቢዎቹ ባሉ የጸጥታ አካላት እና በሌሎች ሰዎች ጥቃት ሊደርስብን ይችላል” በሚል ሥጋት ወደ ቀድሞ ቀያቸው መመለስ እንዳልቻሉ፤
- ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ቦራ ወረዳ የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ያለውን ሁኔታ ሲያስረዱ በራሳቸው ጊዜ ወደ ቀድሞ ቦታቸው የተመለሱ ተፈናቃዮች በታጣቂዎች ታግተው ተወስደው አድራሻቸው እንደማይታወቅ አሁንም ድረስ የጸጥታው ችግር አለመቀረፉን እና በዚህ ሁኔታ ቢመለሱ እነርሱም ለጥቃት እንደሚዳረጉ በመሥጋት ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው ለመመለስ እንደተቸገሩ፤ ከዚሁ ዞን ዱግዳ ወረዳ ከወዮ ገብርኤል ቀበሌ ሙሉ በሙሉ ተፈናቅለው በአጎራባች ከተሞች ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር እየኖሩ ያሉ ተፈናቃዮችን እንዲሁም ከጀዌ ቦፎ እና ኦዳ ፊላ ቀበሌዎች ካላቸው የእርሻ መሬት ይዞታ የተፈናቀሉ ሰዎችን በቋሚነት መልሶ ለማቋቋም እንዲሁም ይዞታቸውን በማስከበር ወደ እርሻ ሥራቸው ለመመለስ የተጀመረ የመልሶ ማቋቋም ሥራ አለመኖሩ፤
- ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን ቡለን ወረዳ ኢማንጅ ቀበሌ ተፈናቅለው ወደቀድሞ ቀያቸው የተመለሱ ተፈናቃዮች አብዛኞቹ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ እንደመሆኑ ለግብርና ሥራ የሚሆን የእርሻ በሬ፣ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ቢሆንም የተመለሱ ተፈናቃዮች የመልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ ባለማግኘታቸው በዘላቂነት ለመቋቋም መቸገራቸው፤
- ከጊቤ 3 የኃይል ማመንጫ ግድብ የተለቀቀው ውሃ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ ለነዋሪዎች መፈናቀል ምክንያት ሆነው ከተለዩ መንስኤዎች መካከል አንዱ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ተፈናቃዮችን በዘላቂነት ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት የበኩሉን አስተዋፆ አለማድረጉ፤
- ከጋምቤላ ክልል አኙዋ ዞን ጆር ወረዳ ኡቱል 01 እና 02 ቀበሌዎች ተፈናቅለው በአሌላ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ ተፈናቃዮች በግጭት ምክንያት ቤት ንብረታቸው ሙሉ በሙሉ በመውደሙና በመዘረፉ እንዲሁም የጸጥታው ሁኔታ አስተማማኝ ባለመሆኑ ወደ ቀያቸው ለመመለስ እንዳልቻሉ፤

- ከአማራ ክልል ወደ አሮሚያ ክልል ተፈናቃዮች ይመለሱባቸዋል በተባሉት አካባቢዎች ያለው የጸጥታ ሁኔታ ከዚህ ቀደም ከነበረው በአንጻራዊነት መሻሻሎች እንዳሉ የሚያሳዩ ሁኔታዎች ቢኖሩም አሁንም ድረስ ለመፈናቀል መንስኤ የነበሩት የጸጥታ ሥጋቶች አስተማማኝ በሚባል ደረጃ እንዳልተቀረፉ እና ተፈናቃዮች ወደ ቀዬአቸው ቢመለሱ በሕይወታቸው ላይ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ለምሳሌ፦ የጸጥታ ሥጋቱ ባለመቀረፉ ከተለያዩ ቀበሌዎች ተፈናቅለው በወረዳ ከተሞች ተጠልለው የሚገኙ ተፈናቃዮች አሁንም ድረስ ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው መመለስ እንዳልቻሉ፤ እንዲሁም አልፎ አልፎ ጥቃት አድራሾች ወደ ከተሞቹ እየገቡ እንደሚወጡ፤ በተወሰኑ ቀበሌዎች ተፈናቃዮች ጥለዋቸው የወጡትን እና ጉዳት ሳይደርስባቸው የቀሩ ቤቶችን እንደሚያቃጥሉ፤ እንዲሁም በአጎራባች ወረዳዎች ለሚመለሱ ተፈናቃዮች ተብለው የተዘጋጁ ጊዜያዊ መጠለያዎችን ማውደማቸው/ማቃጠላቸው፤ በዚህም የተነሳ ተፈናቃዮች በቀጥታ ወደ ቀድሞ መኖሪያ ቀያቸው እንዳልተመለሱ እና ከቀድሞ መኖሪያቸው እርቆ በተዘጋጀ ጊዜያዊ መጠለያ እንዲሰፍሩ መደረጉ፤
- በሶማሊ ክልል ፋፈን ዞን ዱሩዋሌ ቀበሌ በዘላቂነት እንዲሰፈሩ ለተደረጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የተሠሩ መኖሪያ ቤቶች ከተፈናቃዮች ቁጥር ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ ሁሉም ቤት ባለማግኘታቸው ከአንድ በላይ ቤተሰቦች በአንድ ቤት ውስጥ እንዲኖሩ መደረጉ፤
- በጋምቤላ ክልል የወንዞች መሙላትን ተከትሎ በሚከሰት የጎርፍ መጥለቅለቅ በርካታ ሰዎች ከመኖሪያ አካባቢያቸው እንደሚፈናቀሉ እና የጉዳት መጠኑ ይለያይ እንጂ በተደጋጋሚ እና በተከታታይ ለበርካታ ዓመታት እንደሚከሰት፤ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው በመሆኑ የአካባቢው ማኅበረሰብ በክረምት እና በበጋ ወቅቶች በተለያዩ አካባቢዎች ያልተረጋጋ ሕይወት ለመኖር መገደዳቸው፤
- የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ወደ ቀድሞ ቀያቸው በመመለስ በዘላቂነት ለማቋቋም በተለያዩ ክልሎች ጥረቶች የተጀመሩ ቢሆኑም እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች በጣም ውስን ከመሆናቸው ባለፈ በዘላቂ መፍትሔ አተገባበር ወቅት ሊተገበሩ የሚገባቸውን የሰብአዊ መብቶች መርሖች የተከተሉ ባለመሆኑ፤ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በተራዘመ የመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ እንዲቆዩ እና ሰብአዊ መብቶቻቸው እየተጣሱ እንዲቀጥሉ መደረጉ፤ እንዲሁም ተፈናቃዮችን መልሶ በማቋቋም ሂደት በበቂ በጀት ያልተደገፈ መሆኑ በክትትል የተለዩ ክፍተቶቸ ናቸው፡፡


Photo credit: EHRC/Media and Comms/Haleluya Abebe

**WWW.EHRC.ORG**

# ክፍል ፬



# ክፍል አራት

## ማጠቃለያ እና ምክረ ሐሳብ

### ማጠቃለያ

- ኢትዮጵያ በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ለመጠበቅ እና ድጋፍ ለማድረግ የወጣውን የካምፓላ ስምምነትን አጽድቃለች። ይህን ስምምነት ለማስፈጸም ብሔራዊ ረቂቅ ሕግ ቢዘጋጅም ጸድቆ ሥራ ላይ ባለመዋሉ እንዲሁም ለተፈናቃዮች የሚደረጉ የሰብአዊ ድጋፍ እና ጥበቃ እንዲሁም የዘላቂ መፍትሔ ማፈላለግ ሥራዎችን የሚያስተባበር እና በበላይነት የሚመራ ተቋም ባለመኖሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ አሳሳቢ ችግር ሆኖ ቀጥሏል።
- የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ምዝገባ እና ሰነድ የማግኘት መብት ላይ የአሠራር ክፍተት በመኖሩ ለተፈናቃዮች የሚደረገውን ድጋፍ በአግባቡ እንዳይከናወን አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩ በተጨማሪ ተፈናቃዮች የመንቀሳቀስ እና የማኅበራዊ አገልግሎት የማግኘት መብቶቻቸውን ጨምሮ ሌሎች መብቶችን ለመጠቀም እንዳይችሉ አድርጓቸዋል።
- በተወሰኑ አካባቢዎች የተፈናቃዮች መጠለያ/ማቆያ ጣቢያዎች ተገቢውን ጥበቃ ስለማይደረግላቸው የታጠቁ አካላት ሰርገው በመግባት ጥቃት የሚፈጽሙ በመሆኑ ተፈናቃዮች አሥጊ በሆነ የደኅንነት ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።
- በአብዛኞዎቹ አካባቢዎች ወቅቱን የጠበቀ፣ በቂ፣ ያልተቆራረጠ እንዲሁም ልዩ ፍላጎቶች ያሏቸውን ወይም ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ ተፈናቃዮችን መሠረት ያደረገ የምግብ፣ መጠለያ እና ንጹሕ ውሃ አቅርቦት ባለመኖሩ ተፈናቃዮችን ለከፋ ችግር ዳርጓቸዋል። በዚህም ይህንን ክፍተት ለመሙላት እና ሕይወታቸውን ለማቆየት አሉታዊ ውጤት ያላቸው አማራጮችን (negative coping mechanisms) ለመውሰድ ይገደዳሉ። በተጨማሪም ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው አካባቢዎች የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ለተፈናቃዮች ተደራሽ የተደረጉ ቢሆንም በግብአትና በቁሳቁስ እጥረት እና ተያያዥ ችግሮች ሳቢያ ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም። በተለይም ለሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የሚሰጠው የጤና አገልግሎት ድጋፍ በጣም አነስተኛ ነው።
- ከመጠለያ ድጋፍ እጥረት ጋር ተያይዞ ተፈናቃዮች በፀሐይና ዝናብ በተጎዱ የመጠለያ ሸራዎች ውስጥ ለዓመታት ከአንድ በላይ ቤተሰቦች በጋራ በተጣበበ ሁኔታ፤ እንዲሁም በትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ለተለያዩ አገልግሎት በተዘጋጁ መጋዘኖች እና ጅምር ሕንፃዎች ውስጥ የሚኖሩ በመሆኑ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች፤ ለደኅንነት ሥጋት፤ ሴቶች እና ሕፃናትን ደግሞ ለጾታዊ ጥቃት ተጋላጭ አድርጓቸዋል።
- ነዋሪዎችን ከመደበኛ የመኖሪያ ቦታቸው በኃይል ያፈናቀሉ፣ የሰው ሕይወት ያጠፉ፣ ንብረት ያወደሙ፣ አካላዊ ጉዳት ያደረሱ ቡድኖች እና ሰዎች በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ በቂ እርምጃዎች አለመወሰዳቸው፤ የሕግ የበላይነትን፣ ተጠያቂነትን እና የተፈናቃዮች ፍትሕ የማግኘት መብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን የሚያሳድር ሲሆን፤ በዘፈቀደ/በኃይል ለሚደረግ ሰዎችን የማፈናቀል ተግባር የሚወሰዱ አስተማሪ እርምጃዎች (actions that have deterrence effect) እንደሌሉ ማሳያ ነው። ይህም በሀገሪቱ ያለው ማንነትን መሠረት ያደረገ ሰዎችን በኃይል በማፈናቀል ሰብአዊ እና ቁሳዊ ጉዳት የማድረስ ተግባር ተባብሶ እንዲቀጥል አድርጎታል።

- በተወሰኑ ክልሎች የተጀመሩ የዘላቂ መፍትሔ አማራጭ ዕቅዶች እና መርኃ ግብሮች የሚበረታቱ ቢሆንም አተገባበራቸው የሰብአዊ መብቶች መርሖችን ያልተከተሉ በተለይም የመፈናቀል ምክንያት የሆኑት የደኅንነት ሥጋቶች ባለመወገዳቸው፣ ተፈናቃዮችን እና ተቀባይ ማኅበረሰብን ባለማሳተፉ፣ የተፈናቃዮችን ፍላጎትና ፈቃድ ያላገናዘበ እንዲሁም የተፈናቃዮችን ቤት፣ መሬት እና ንብረት መብቶች ከግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ ተፈናቃዮችን በዘላቂነት ለማቋቋም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረም። በዚህም በርካታ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔ ሳያገኙ በመጠለያ ጣቢያዎች እና ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው መኖር ከጀመሩ ዓመታትን ያስቆጠሩ በመሆናቸው በተራዘመ የመፈናቀል ሁኔታ ውስጥ እንዲኖሩ ተደርገዋል።

# ምክረ ሐሳቦች

***የሕግ ማዕቀፍን እና ተቋማዊ አደረጃጀትን በተመለከተ፡-***

- የካምፓላ ስምምነት ማስፈጸሚያ ብሔራዊ የሕግ ረቂቅ መንግሥት ልዩ ትኩረት በመስጠት በተፋጠነ ሁኔታ እንዲያጸድቅና ተግባራዊ እንዲያደርግ፤ መፈናቀልን ለመከላከል የሚያስችል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት መቅረጽን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎች እንዲወስዱ፤

***ምዝገባ እና ሰነድ የማግኘት መብትን በተመለከተ፡***

- የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶታቸውን መጠቀም እና መተግበር እንዲችሉ አስፈላጊው ምዝገባ እንዲደረግላቸው፤ የግል መታወቂያ፣ የወሳኝ ኩነት ሰነዶችን እና ፓስፖርት እንዲያገኙ ወይም በመፈናቀል ሂደት የጠፉ ወይም የተበላሹ ሰነዶቻቸው እንዲተኩላቸው ባሉበት ቦታ አስፈላጊው ሁኔታዎች እንዲመቻቹላቸው፤

***የጸጥታ፣ ደኅንነት እና ፍትሕ የማግኘት መብትን በተመለከተ፡-***

- የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የተጠለሉባቸውን ቦታዎች የሲቪልና የሰብአዊነት ባሕሪ እንዲከበር፤ መንግሥት የታጠቁ ቡድኖች ወይም አካላት ወደ እነዚህ ቦታዎች ሰርገው በመግባት ጥቃት እንዳይፈጽሙ ተገቢውን ጥበቃ እና ክትትል እንዲያደርግ፤ እንዲሁም ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ተፈናቃዮችን ለተጨማሪ የመብት ጥሰት የሚዳርጉ ሁኔታዎችን ትኩረት ሰጥቶ በየጊዜው በመከታተል እና በመለየት አስፈላጊውን የደኅንነት እርምጃ እንዲወስድ፤
- የተፈናቃዮችን የመንቀሳቀስ እና የመኖሪያ ቦታን የመምረጥ መብትን የሚገድቡ ሁኔታዎችን መቅረፍ፣ እንዲሁም በመብቱ ላይ ገደብ የመጣል ውጤት ያላቸውን ተመጣጥኝ፣ አስፈላጊ እና ሕጋዊ ያልሆኑ ውሳኔዎችን በመከለስ ተፈናቃዮች በመብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ መንግሥት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ፤
- በኃይል ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ፍትሕ የማግኘት መብታቸው እንዲከበር፤ ያፈናቀሉ፣ ሕይወት ያጠፉ፣ የአካል ጉዳት ያደረሱ፣ ንብረት የዘረፉ እና የተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በመፈጸም ተሳታፊ የነበሩ አጥፊዎችን በየደረጃው የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል የፍትሕ አካላት በሕግ ተጠያቂ እንዲያደርጓቸው፤

***የሰብአዊ ድጋፍና ማኅበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦትን በተመለከተ፡-***

- *መንግሥት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ እስከሚቻለው ባለመዘግየት በቂ ምግብና ውሃ፣ መጠለያ፣ የሕክምና እና የጤና አገልግሎቶች፣ ንጽሕና፣ ትምህርት እና ሌሎች አስፈላጊ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ያካተተ በቂ የሰብአዊ ድጋፍ የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በማስተባበር እንዲያቀርብ፤ ተገቢ ሆኖ ሲገኝም እነዚህን ድጋፎች ለተቀባይ ማኅበረሰብም እንዲያደርስ፤*

***ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተፈናቃዮች በተመለከተ፡-***

- ልዩ ድጋፍ ለሚስፈልጋቸው ተፈናቃዮች በተለይም ከቤተሰባቸው ለተለዩ እና ጠባቂ ለሌላቸው ሕፃናት፣ ለሴት የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች፣ ለነፍሰጡሮች፣ ጨቅላ ሕፃናት ላሏቸው እናቶች፣ ለአረጋውያን እና ለአካል ጉዳተኞች ወይም የማይድን/ቋሚ ሕመም ላለባቸው ተፈናቃዮች ልዩ ጥበቃ እና ድጋፍ እንዲደረግላቸው፤ ለተፈናቃይ ሴቶች የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት እንዲሁም ወሲባዊ እና ሌሎች ተያያዥ ጥቃቶች ለደረሰባቸው ተገቢው የሥነ ልቦና እና ማኅበራዊ ድጋፍ እንዲደረግላቸው፤

***የዘላቂ መፍትሔዎች አተገባበርን በተመለከተ፡-***

- መንግሥት እንደ አስፈላጊነቱ ለጋሽ ድርጅቶችን በማስተባበር ጭምር የተፈናቃዮችን ደኅንነትና ሰብአዊ ክብር በጠበቀ ሁኔታ እንዲሁም በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የዘላቂ መፍትሔ አማራጮችን ተግባራዊ እንዲያደርግ፤ እንዲሁም የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ተፈናቃዮች በዘላቂነት ለመቋቋም ስላሏቸው አማራጮች በመረጃ ላይ ተደገፈው መመረጥ እንዲችሉ እንዲያደርግ፤
- ወደ ቀድሞ መኖሪያ ቀያቸው የተመለሱ ወይም ሌላ ቦታ የሰፈሩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በዘላቂነት ተቋቁመው እራሳቸውን ማስተዳደር እስኪችሉ ድረስ መንግሥት በቂ፣ ወቅቱን የጠበቀ እና ተደራሽ የሆነ የሰብአዊ ድጋፍ እንዲያቀርብ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ተደራሽ እንዲያደርግ፤ በተጨማሪም መንግሥት የተፈናቃዮችን ንብረት እና ይዞታ ማስከበር፤ የወደሙ መኖሪያ ቤቶችን መጠገን/መሥራት እና የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን ወደነበሩበት በመመለስ ተደረሽ እንዲያደርግ፤
- የመንግሥት ዘላቂ መፍትሔ ዕቅዶች እና መርኃ ግብሮች የተፈናቃዮችን የቤት፤ መሬት እና ንብረት መብቶች ከግምት ውሰጥ እንዲያስገባ፤ በተለይም ከመሬታቸው ጋር ልዩ ጥገኝነትና ቁርኝት ያላቸው ተፈናቃዮች ወደቀድሞ ቀያቸው በሚመለሱበት እና በሚቋቋሙበት ወቅት በሌሎች ሰዎች ወይም በመንግሥት አካላት የተያዘባቸው መሬት እንዲመለስላቸው ወይም ምትክ እንዲሰጣቸው በተቻለ መጠን አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በሙሉ እንዲወሰዱ፤ ወደሌላ አካባቢ ተዘዋውረው እንዲሰፍሩ ሲደረግም የተፈናቃዮችን የቀድሞ አኗኗር ሁኔታ ከግምት ውስጥ እንዲያስገባ፤
- በተለያዩ መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ እና ለመመለስ በሂደት ላይ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ወደተፈናቀሉበት ቦታ እንዲመለሱ ከመደረጉ አስቀድሞ የክልል እና የፌዴራል የመንግሥት አካላት ተቀናጅተው በአካባቢዎቹ የሚስተዋሉ የጸጥታ ሥጋቶችን አስተማማኝ በሚባል ደረጃ መቀረፋቸውን እንዲያረጋግጡ እና የሕግ የበላይነት እንዲያስከብሩ፤ ለተመለሱት ተፈናቃዮችም በአካላቸው እና በንብረታቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጥቃት ለማስቀረት ተገቢው ጥበቃ እንዲደረግላቸው፤

***የአደጋ ሥጋት ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና የአደጋ ምላሽ በተመለከተ፡-***

- በተፈጥሮ አደጋ በተለይም በጎርፍ አደጋ ሳቢያ የሚከሰተውን መፈናቀል እና የሰብአዊ ቀውስ ለመቀነስ መንግሥት በትምህርት እና ጤና ተደራሽነት እንዲሁም በግብርና

ምርቶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ አስቀድሞ በመተንበይ እና በማቀድ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ፤ የትምህርት፣ የጤና፣ የግብርና እና ሌሎች መሠረተ ልማቶች ሲገነቡም አካባቢያዊ ሁኔታን ታሳቢ ያደረጉ እና የአደጋ ሥጋትን በተለይም የጎርፍ አደጋን በዘላቂነት መቋቋም የሚችሉ መሆን አለባቸው።